# የሕይወት ሽግግሮች የጋራ ትዕምርቶች ትንተና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ

*ሥራዬ እንዳለው ውበቴ[1]፣ ዋልተንጉሥ መኮንን[2]፣ ደስታ አማረ[3]*

**አኅጽሮተ ጽሑፍ**

ይህ ጥናት በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ዘንድ የሕይወት ሽግግሮችን (ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት) ምክንያት በማድረግ በሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች (Rituals) ላይ ተደጋግመው የሚታዩ የጋራ የሆኑ ትዕምርቶችን (Symbols) መመርመር ላይ ያተኮረ ነው። የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች (Rites of Passage) ሲከበሩ መልካቸውን እየለዋወጡ የሚመጡና፣ በወቅቱ የሚገለጡ ትዕምርቶች መኖራቸው ሲሆን እነዚህንም ጉዳዮች በወጉ ያጠና ጥናት አለመኖሩ ነው። የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ሲከበሩ ተደጋግመው የተገለጡ የጋራ ትዕምርቶችን መተንተን ነው። ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ ቀዳማይ መረጃዎች ተጠኚው ማህበረሰብ ከተካለለባቸው አርባ አንድ ቀበሌዎች ውስጥ ስድስቱ በዓላማ ተኮር የንሞና ስልት የተመረጡ ሲሆን፣ አስር ሰዎች ደግሞ በቁልፍ መረጃ ሰጭነት ተሳትፈዋል። የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ሲከናወኑ በመመልከትና ቃለ መጠይቅ በማካሄድ ተሰብስበዋል። ካልዓይ መረጃዎች ደግሞ ልዩ ልዩ ቤተ መጻሕፍትን፣ ድረ ገጾችንና ሰነዶችን በመጠቀም ተገኝተዋል። የጥናቱን መረጃዎች ለመተንተን ከተግባራዊ፣ ከመዋቅራዊ-ተግባራዊ እና ከፍካሬ ልቡናዊ ንድፈ ሀሳቦች ለዓላማዎች ተስማሚ የሆኑ ሀሳቦች ተመርጠው በማሕቀፍነት ተጠቅሟል። የተተነተነው መረጃ እንደሚያሳየው የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች (ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት) የማህበረሰቡ እሴትና መዋቅር የሚገለጥባቸው፣ ተጠናክረውና ተጠብቀው የሚቀጥሉባቸው የሕይወት ዘመን ክስተቶች ናቸው። በአከባበር ሂደታቸው ወቅት በተለይ ሽግግሩን የሚያካሂደው ባለጉዳይ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያስፈልገው መሆኑ፣ ማህበራዊነት ጎልቶ የሚታይባቸው እና የሰላምና የእርቅ ማውረጃና ማወጃ አጋጣሚዎች እንዲሁም የልዩ ልዩ መስዋዕት ማቅረቢያ ሁነቶች መሆናቸውን ማጤን ተችሏል። በተጨማሪም በጭንቀትና በስጋት የታጀቡ ሁነቶች መሆናቸው ሶስቱንም የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ያስተሳሰሩ ትዕምርቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

ቁልፍ ቃላት፡- [የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች፣ ሥርዓተ ክዋኔ፣ ትዕምርት]

## 1. መግቢያ

ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ለዘመናት የተከማቹ ባህላዊ ጥበቦች የሚጠኑበት የትምህርት ዘርፍ እንደሆነና አራት ዘውጎች እንዳሉት (Dorson 1972፡232) ያስረዳሉ። እነሱም ሥነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ሲሆኑ ከመስክ በሚሰበሰቡ መረጃዎች አማካኝነት እንደሚጠኑ ከላይ የተጠቀሱት ምሁር ገልጸዋል። አንድ ማህበረሰብ በልማድ ከሚከውናቸው ሀገረሰባዊ ልማዶች ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ናቸው።

---

[1]በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በፎክሎር ዘርፍ የሦስተኛ ዲግሪ ዕጩ፣ የኢሜል አድራሻ siraye3195@gmail.com
[2]በፎክሎር ዘርፍ Ph.D፣ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ የፎክሎር መምህርና ተመራማሪ፣ ኢሜል፡ nigus2020@gmail.com
[3]በፎክሎር ዘርፍ Ph.D፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የባህል ዘርፍ ተመራማሪ፣ ኢሜል፡ desta_amare@yahoo.com

የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶችን በ1909[4] "*Les rites de passage*" በሚል ርዕስ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ለህትመት በማብቃት ጽንሰ ሀሳቡን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁት የስነሰብ ተመራማሪው Arnold van Gennep ናቸው። ይህ ስራ በ1960 "The Rites of Passage" በሚል ርዕስ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ታትሞ ቀርቧል። በዚህ ስራ ላይ ተጠቅሶ እንደምናገኘው በሕይወት ዘመን በሂደት የሚያጋጥሙ እንደ ወሊድ፣ ጋብቻ፣ ሞት እና ሌሎች ሁነቶች እንደ ድልድይ ሆነው አንዱን ከሌላው የማገናኘት ሚና አላቸው ይላሉ (Gennep 1960፡1-3)። አክለውም የሕይወት ሽግግሮች ባለጉዳይን[5] ከአንድ ግላዊና ማህበራዊ ደረጃ ወደ ቀጣዩ እንደሚያሸጋግሩና በሽግግሩ ወቅትም ልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች እንደሚፈጸሙ አስረድተዋል (Gennep 1960:X)።

የሕይወት ሽግግሮችን በአንድላይ ያጠኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ትኩረታቸው በወሊድ፣ በጋብቻ እና በሞት ወቅት የሚከናወኑ ሥነ ሥርቶችን መግለጽ፣ የአከባበር ቅደም ተከተላቸውን መዘርዘር እንዲሁም የቀጠሉና የተለወጡ ባህላዊ ጉዳዮችን ማመላከት ነው አፀደ (2007 ዓ.ም)፣ ደስታ (2007 ዓ.ም)፣ ሥራዬ (2005 ዓ.ም)፣ ድርብወርቅ (2007 ዓ.ም)። እነዚህ ጥናቶች የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የየራሳቸው ምዕራፍ ተመድቦላቸው የቀረቡ በመሆናቸው የሽግግሮችን የእርስበርስ ትስስር አያሳዩም። የሕይወት ሽግግሮችን ከ Gennep ሶስቱ የመዋቅር ደረጃዎች አንጻር ለመመደብ በመሞከር የደስታ (2007 ዓ.ም) እና የሥራዬ (2005 ዓ.ም) ጥናቶች ይጠቀሳሉ።

የሕይወት ሽግግሮችን ከማጥናት አንጻር አጸደ (2007 ዓ.ም) ጥናት የዋግ ኽምራ አስተዳደር ዞን ህብረተሰብ የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓቶች ክዋኔያቸው በዘመናዊነትና በሉላዊነት ሰበብ ሙሉ በሙሉ ሳይለወጥና ሳይጠፉ አውዳቸውን መሰረት በማድረግ በመቅረጸ-ምስል፣ ድምጽና በፎቶ ካሜራ መረጃ በመሰብሰብ አሁን ባለበት ሁኔታ የሚገኘውን ባህል እንዲሰነድ የሚል ነው። ይህ ጥናት የሕይወት ሽግግር ሥርዓተ ክዋኔዎችን አጥንቶ የሚገለጡ እውቀቶችን ከማሳየት ይልቅ ባህሉን መሰነድ ላይ አተኩሯል አጸደ (2007 ዓ.ም)።

ድርብወርቅ (2007 ዓ.ም) በጉምዝ ብሔረሰብ የሚከወኑ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓትን በማሳየት ከሚከወኑባቸው አውዶች አንፃር የሚኖራቸውን ፋይዳ አጥንተዋል። የዚህ ጥናት የትንተና ክፍል የውልደት ሥርዓት (ቅድመ ውልደት፣ የውልደት ጊዜ እና ድህረ ውልደት) በሚል በወቅቱ የሚከናወኑ ባህላዊ ልማዶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል። የጋብቻ ስርዓቱን በተመለከተ ደግሞ በብሔረሰቡ የታወቁ የጋብቻ አይነቶች ተብራርተውበታል። የመጀመሪያ የወር አበባ እና የወንድ ልጅ ግርዛት ሥርዓቶችም የተለየ አከባበር እንዳላቸው በዚህ ጥናት ተመላክቷል። እንዲሁም የሀዘን እና የተስካር ሥርዓት በብሔረሰቡ ምን እንደሚመስል ተገልጿል።

ከሕይወት ሽግግሮች ውስጥ ወሊድ እና/ወይም ጋብቻ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል የወሊድና የገለብ ሥነ ሥርዓት በሚል በአክሱም አካባቢ በምን ዓይነት ሥነ

---

[4]በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋሉ የውጭ ምንጮች የተጠቀሱት እ.ኤ.አ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ምንጮች ደግሞ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሲሆን ከህትመት ዘመናቸው ዓ.ም የሚል አለባቸው፡፡

[5]ባለጉዳይ የሚለው ቃል በዚህ ጥናት አንድ ሽግግር እና ለውጥ የሚያካሂድ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ይወክላል፡፡ ቃሉን የተዋስኩት ከጥላሁን ተሊላ (2007 ዓ.ም) ጥናት ነው፡፡

ሥርዓቶች እንደሚከበሩ መለሰ (2000 ዓ.ም) በጥናታቸው አሳይተዋል። እንዲሁም የሴት ልጅ ያለዕድሜ ጋብቻ በመደበኛ ትምህርታቸው፣ በግልና በማህበራዊ ሕይወታቸው፣ ከፍ ሲልም በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አኳኋን ላይ ያስከተለውን ተጽእኖ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን (Guday 2005) በጥናታቸው አመላክተዋል።

በሌላ በኩል ሥርዓተ ክዋኔዎች ለተጋቢዎች የሚና ሽግግር ለማድረግ እንደሚያግዟቸው በኒዘርላንድ የተለመዱ ልዩ ልዩ የጋብቻ ዓይነቶችን በመተንተን ያመላከተ ጥናትም ተጠቃሽ ነው (Kalmijn 2004)። ይህ ጥናት በውስጡ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሙሽሮች ለሚያካሂዱት የሚና ሽግግር ባይተዋር በመሆናቸው የሚሰማቸው ጥርጣሬ እንዲቀንስ ያግዛሉ የሚል ሀሳብ ይዟል። በተጨማሪም የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች የሙሽሮችን የወደፊት እጣፋንታ መወሰኛ ተደርገው እንደሚወሰዱም ያትታል። በመሆኑም በሰርጉ ሥነ ሥርዓት ሙሽራውም ሆነ ሙሽሪት የትዳር አጋራቸውን ለጓደኞቻቸውና ለዘመድ አዝማዳቸው የሚያስተዋውቁበት ወግ ማዕረግ እና አብረው መኖር የሚጀምሩበት መሆኑን የሚያበስሩበት በመሆኑ በአብሮነት ለመዝለቅ ጉልህ ሚና አለው ይላሉ።

ጋብቻ ተጋቢዎች ወሳኝ ለውጥ የሚያካሂዱበት በመሆኑ በኃይል አስገዳጅነት ጭምር የአመለካከት ለውጥ የሚያደርጉበት መሆኑን (Kitahara 1974) ገልጸዋል። ተጋቢዎች ከተቀላቀሉበት ማህበራዊ ደረጃና ከሚኖሩበት ማህበራዊ አካባቢ ለሚመነጩ ደንቦች ያድራሉ፤ ይገዛሉ፤ ራሳቸውን ያስማማሉ የሚል ሀሳብ አክለዋል። ለዚህ የሚበቁትም በወቅቱ በሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች አማካኝነት መሆኑን አጽንኦት ሰጥተዋል። ከላይ የቀረቡት ጥናቶች በልዩ ልዩ የሕይወት ሽግግሮች ወቅት የሚከወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለሽግግሩ ስምረት አዎንታዊ ሚና እንደሚያበረክቱ የሚያሳዩ ናቸው።

በሌላ በኩል ከሰው ልጅ የሕይወት ዘመን ጋብቻ፣ አራስነት እና እርጅና የሽግግር ጊዜ በመሆናቸው ባለጉዳዮች ለጭንቀትና ለግራ መጋባት የሚዳረጉባቸው፣ ከራሳቸው የሚለዩበት፣ እርጋታ የሚያጡበት ጊዜ ነው ሲሉ (ዋልተንጉሥ (2007 ዓ.ም) ገልጸውታል። በመሆኑም አቅም የሚያሳጣቸው በመሆኑ ለክፉ ዓይን አጋላጭ አውዶች ናቸው በማለት የወቅቱን አሳሳቢነት አስረድተዋል። ይህም የሕይወት ሽግግሮች በሥርዓተ ክዋኔዎች የሚታጀቡት ምናልባት የባለጉዳዮችን ደህንነት ለመጠበቅ ይሆናል የሚል መላምት ያጭራል።

ሽግግርን ከቱለማ ኦሮሞ የጊዜና የቦታ አምድ አንጻር በመመርመር በወቅቱ የሚታዩ የሽግግር መገለጫዎችን በማሳየት ረገድ ጥላሁን (2007 ዓ.ም) ጥናት ተጠቃሽ ነው። በመርሣ (በሽግግር) ወቅት የተከበሩ ሰዎችን በዘፈን ግጥሞች መዝለፍና ማዋረድ፣ በዘወትር የማይነኩ የብልግና ቃላትን በአደባባይ እንደልብ መጠቀም፣ ስህተት ነው ያሉትን በግልጽ መተቸት፣ ወዘተ. ይከናወናሉ። እነዚህ ተግባራትና ምግባራት በዘወትሩ ያልተለመዱ፤ በመርሣው ወቅት ግን በነጻነት የሚገለጹ በመሆናቸው ወቅቱ በአዳዲስና በእንግዳ ነገሮች የተሞላ መሆኑን ማሳያ ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

በአጠቃላይ ከላይ ቅኝት የተካሄደባቸው ጥናቶች እንደተጠኑባቸው ዓላማ እና እንደ ጥናቱ ደረጃ ልዩ ልዩ ቁምነገሮችን አንስተዋል። ሆኖም ፍጹምና ምሉዕ ናቸው ማለትም አይቻልም። ይህም ከአጠናን አንጻር፣ ከትኩረት ነጥቦችና ከጥናት ዓላማ መለያየት ሊመጣ ይችላል። የሆነው ሆኖ

የሕይወት ሽግግሮችን (ወሊድ፣ ጋብቻ፣ ሞት) በአንድ ላይ መይም ከሶስቱ አንዱ ላይ ብቻ ትኩረታቸውን በማድረግ የተሰሩት ጥናቶች የክዋኔዎቹን ቅደም ተከተል ማሳየት፣ መቀረስ (በቅርስነት ማቆየት)፣ በክዋኔያቸው የቀጠሉና የተለወጡ ሥርዓተ ክዋኔዎችን መዘርዘር ላይ ብቻ ትኩረታቸውን ያደረጉ ናቸው። የሕይወት ሽግግሮች ሥርዓተ ክዋኔዎች ላይ የታዩ የጋራ ትዕምርቶችን እና ያላቸውን ትስስር አላሳዩም። በመሆኑም ይህ ጥናት እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ሲባል የተካሄደ ነው።

ይህንን ጥናት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማድረግ መነሻ የሆነው ምክንያት ለጥናት በተመረጠው አካባቢ በወሊድ፣ በጋብቻና በሞት ወቅት የሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሲከናወኑ አይነታቸውን እየለዋወጡ ተደጋግመው የሚመጡ ትዕምርቶች መኖራቸው አሉ። እነዚህም የማህበረሰቡ እውቀት፣ አመለካከት፣ የሕይወት ፍልስፍና እና ርዕዮተ ዓለም የሚያሳዩ በመሆናቸው የዚህ ጥናት ትኩረት ሆነዋል። በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ወቅት የተገለጡ የጋራ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው? የትዕምርቶቹ ይዘት ምንድነው? የሕይወት ሽግግሮች ትስስር ምን ይመስላል? ለሚሉ የምርምር ጥያቄዎች መልስ አስገኝቷል።

የጥናቱ ዋና ዓላማ በወሊድ፣ በጋብቻና በሞት ወቅት የሚገለጡና ተደጋግመው የሚመጡ ትዕምርቶችን መተንተን ሲሆን በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ወቅት የታዩና የተገለጡ ተመሳሳይ የሆኑ ትዕምርታዊ ቁሶችን፣ ሃሳቦችን፣ ሁኔታዎችን እና ቁጥሮችን የጋራ ባህሪያት መመርመር፣ ከዚህ በመነሳት የሕይወት ሽግግሮችን ትስስር መግለጽ የሚሉ ዝርዝር አላማዎችም አሉት።

## 2. ንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፎች

የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረት ትዕምርት እንደመሆኑ መጠን ትዕምርቶችን ከሥርዓተ ክዋኔዎች ጋር ሊያስተሳስሩ የሚችሉ ተስማሚ ንድፈ ሀሳቦችን በመረጃ መተንተኛነት ተመርጠዋል። እነሱም ከተግባራዊ (Functionalism)፣ ከመዋቅራዊያን-ተግባራዊያን (Structural-Functionalism) እና ከፍካሬ ልቡናዊያን (Psycho Analysis) ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ ተስማሚ የሆኑ ሀሳቦችን ተጠቅሟል።

ከተግባራዊያን መካከል Malinowski እንደገለጹት አንድ ሰው ለመኖር ሊሟሉለት የሚገቡ መሰረታዊ ነገሮችን ለማግኘት በባህሉ ውስጥ የሚተገበሩ ትዕምርታዊ ሥርዓቶች (እንደ ሃይማኖት፣ እምነት እና እሴቶች) የየራሳቸውን ሚና ይወጣሉ። እነዚህም የባህል ልዩ ልዩ ትዕምርቶች በሥርዓተ ክዋኔዎች ይተላለፋሉ። ትዕምርቶች አንድን እውቀት ወይም ደንብ መግለጫ መሳሪያ ወይም የተግባቦት መንገድ ናቸው። ለምሳሌ ፖለቲካዊ ትዕምርቶች የኃይልና የስልጣን መሳሪያዎች ናቸው (Malinowski in Firth 1973)።

ይህንን ሀሳብ በመጋራት ትዕምርቶች ከማህበረሰቡ ሂደት ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው፣ ከሚፈጸሙበት ጊዜ እና ከሁነቶች ቅደምተከተል ነጥሎ መተንተን አይቻልም (Turner 1974:20)። ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የሥርዓተ ክዋኔ ትዕምርቶች በማህበራዊ ድርጊቶች ላይ የራሳቸውን አሻራ ያሳርፋሉ። እንደ Firth (1973) ገለጻ ትዕምርቶች አቅም ያላቸው የመረጃ አህዶች መከማቻ ሲሆኑ አስፈላጊነታቸውም ሥርዓተ ክዋኔን ከነአውዱ ለመረዳት ያስፈልጋሉ በማለት ይገልጻሉ።

ይህንንም (Turner cited in Pentikainen 1979:159) በሶስት የትንታኔ ደረጃዎች ከፋፍለው አሳይተዋል። እነሱም ከዋኞች ለክዋኔው የሚሰጡትን ፍች መግለጥ (an exegetical)፤ ከክዋኔው አውድ በመነሳት ትዕምርቶችን የማውጣት ጥበብ (an operational) እና ነገሮችን በማወዳደርና በማነጻጸር የሚገኝ ፍች (the positional meaning) የሚሉ ናቸው።

ትዕምርቶች በአንድ ቡድን አባላት መካከል ባለ ሁኔታዊ መስተጋብር ይገለጣሉ። በዚህ መሰረት ሀሳቦች ትዕምርታዊ ባህሪያት እና ፍች የሚኖራቸው በሂደት መሆኑን ያስረዳሉ። በጊዜ ሂደትም ባህል ውስጥ ገብተው በሰው ሰውነት ላይ ሰልጥነው ይታያሉ። ትዕምርቶች ልቅነትን (ገደብ አልባነትን) ለመቆጣጠር፣ ለተጨማሪ የመረጃ ምንጭ ከመሆናቸውም ባሻገር ያላወቁትን ውስጣዊ ችሎታ እና ውጫዊ ማንነት የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው ማለት ይቻላል። የሰውነት ባህሪ የተገነባው በባህል በተቃኘ ፍልስፍና አማካኝነት ነው። የፍች ስርዓታቸው የተዋቀረውም ከሕይወት ልምድ በሚቀሰሙ ቅርጾች፣ ደንቦች፣ ጭብጦችና አቅጣጫዎች ነው (Pentikainen 1979:161)።

በተግባራዊያን-መዋቅራዊያን ዕይታ ማንኛውንም ሥርዓተ ክዋኔ ለመተንተን የሚያስችሉ ደንቦችን በመዋቅሩ ውስጥ ተደጋጋሚ የሆኑ፣ በተለያዩ የሥርዓተ ክዋኔ አይነቶች ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ ትዕምርቶችንና አካላዊ ገለጻዎችን መለየት ያስፈልጋል። በዚህም በተለያየ ጊዜና ሁኔታ የሚከወኑ ሥርዓቶች ተመሳሳይ ቅርጽና ይዘት ወይም ተመሳሳይ ትርጓሜ ሊያስገኙ የሚችሉ ትዕምርቶችን ማውጣት ይቻላል። የሥርዓተ ክዋኔን ስርዓታዊ እና ተዋረዳዊ አካሄድ ለማሳየት ከማዕከላዊነት፣ ከቃላዊ ማንነትና ከምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ መዋቅር፣ ፍልስፍናዊ አቋምና ሃይማኖታዊ ዕይታዎች ወሳኝ ናቸው። እነዚህ ማህበረ-ባህላዊ ተላውጦዎች ሥርዓተ ክዋኔውንና ማህበረሰቡን በቀላሉ እንድንረዳው የሚያደርጉ ግብአቶች ናቸው (Bell 1997)።

የፍካሬ ልቡና ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኝ እንደሆኑ የሚነገርላቸው Sigmund Freud (1856-1939) ትኩረታቸው የሰው ልጅ አዕምሮ አፈጣጠርና ባህሪ ላይ ነው። ንድፈ ሀሳቡ የሰው ልጅን የታመቀ ስሜት፣ የኢ-ንቁ እና የተደበቁ ሀሳቦችን የመፈከር እውቀት እንደሆነ ይነገራል (Cohen 1969)። Freud እና ተከታዮቻቸው ሥርዓተ ክዋኔ መሰረታዊ ከሆነ የሰው ልጅ ባህሪያት እንደተወሰደ እንዲሁም ትዕምርቶችና ጭብጦች የተዋቀሩት ከሰው ልጅ ድብቅ ከሆነው የአዕምሮ ክፍል ነው የሚል አቋም አላቸው። ይህንንም ለማወቅ ሰው አስቦና ተጠንቅቆ ከሚያወራው (ግልጽ ከሆነው) የአዕምሮ ክፍል ትዕምርቶችን በመተርጎም ድብቁ አስተሳሰብ ላይ መድረስ እንደሚቻል እና ድብቁ የአእምሮ ክፍል ውስጥ የቀመጡ፣ የተተው፣ የተሸሹ፣ የተለወጡ፣ የተካዱ ነገሮች መገለጫ ባህሪያት መሆናቸውን ገልጸዋል።

Jung (1956) እንደሚሉት ከሆነ በኢ-ንቁ (ድብቅ የሆነው) የአእምሮ ክፍል ውስጥ ያለው ትዕምርታዊ መዋቅር የማህበረሰቡ ወይም የግለሰቡ እውነታ ነው። አንዳንዶቹ እውነታዎች የሁሉም ሰው ባህሪ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ በቤተሰብ፣ በማህበራዊ ቡድን ላይ ሊታዩ መቻላቸውን ገልጸዋል። በሚቶችና በሥርዓተ ክዋኔዎች ውስጥ ተደጋግመው የሚመጡ የመባያ ጉዳዮችን በተከወኑባቸው አውዶች በመመርመር የሁሉም ሰው የጋራ ባህሪ (ሁለንተናዊ የኢ-ንቁ ባህሪያት ስብስብ) (universal characterstics of the collective unconcious) ማህበረሰቡ በሚፈጽማቸው ልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች ላይ ተደጋግመው እንደሚታዩ ገልጸዋል።

ከላይ እንደተገለጸው ሥርዓተ ክዋኔ ግልጽ ወይም ንቁ በሆነው የአዕምሮ ክፍል የሚቀርብ ቢሆንም በሚከወኑ ትዕምርቶች አማካኝነት ድብቁ (ኢ-ንቁ) የአዕምሮ ክፍል ውስጥ ያሉ ፍላጎቶችንና ግጭቶችን ይገልጻሉ። እዚህ ላይ ለመድረስ ሶስት የትንታኔ መንገዶችን መጠቀም እንደሚቻል (Frued 1931) ጠቁመዋል። የመጀመሪያው አንድን ትዕምርት ወስዶ ዝምድና ያላቸው ብዙ ሀሳቦችና ስሜቶች ማደሪያ በማድረግ (Condensation) የሚካሄድ ነው። ሁለተኛው አንድን ሀሳብ ወይም ስሜት ሙሉ በሙሉ በመለወጥ (Displacement) የሚሰጥ ትንታኔ ሲሆን ሶስተኛው አንድን ነገር ጥሩ ወይም መጥፎ ወደሆኑ ነገሮች መከፋፈል (Splitting) ላይ ያተኩራል። በነዚህ ዘዴዎችም በሥርዓተ ክዋኔዎች የተገለጡ ትዕምርቶችን በመመርመርና ፍች በመስጠት የሰው ልጅ ድብቅ አስተሳሰብ ላይ መድረስ እንደሚቻል ይገልጻሉ (Cohen 1969)።

ይህ ጥናትም በሕይወት ሽግግር ሥርዓተ ክዋኔዎች ተደጋግመው+ የተገለጡ ትዕምርቶችን ምንነት ለመረዳት የተግባራዊያን፣ የሥርዓተ ክዋኔዎችን መዋቅር ለማጤን የመዋቅራዊያን ተግባራዊያን እንዲሁም የትዕምርቶችን ፍች ለመረዳትና ለመግለጽ የፍካሬ ልቡናዊያን ንድፈ ሀሳቦችን እንደ አስፈላጊነታቸው ተጠቅሟል።

## 3. ጽንሰ ሀሳባዊ ሀሳቦች

### 3.1. የሥርዓተ ክዋኔ ምንነት

የሥርዓተ ክዋኔ ጥናት አባት የሆኑት Van Gennep (1909/1960) እንደገለጹት ሰዎች በሥርዓተ ክዋኔ የታጀበ የደረጃ ለውጥ ለማከናወን ባለ ሶስት እርከን መዋቅሮችን (መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል) እንደሚያልፉ ገልጸዋል። ቀጥሎ የጥናት መስኩን የተቀላቀሉት የስነ ሰብ ተመራማሪ Turner ሲሆኑ የGennepን ባለሶስት እርከን የመዋቅር ንድፈ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ሥርዓተ ክዋኔ ድራማዊ መዋቅር ያለው የማህበረሰብ ሂደት ነው ይላሉ (Turner 1969:95)። በተጨማሪም (Canda 1988:209) Gennepን ጠቅሰው እንደጻፉት ሥርዓተ ክዋኔ የነበረን ሁኔታ የመለወጥ ሂደት ብቻ ሳይሆን ለውጥን የማረጋገጥና የመጠበቅ ሂደት ጭምር እንደሆነ ይገልጻሉ። ለዚህም ዋነኛ ምሳሌዎች የሕይወት ዑደቶች ናቸው።

ሥርዓተ ክዋኔን ካጠኑ ምሁራን መካከል የሚጠቀሱት Cathrine Bell ጉዳዩን ቃላዊ ያልሆነ፣ ነገር ግን እንደ ስነልሳናዊ ጉዳዮች በርካታ ትዕምርቶች ያሉበት፣ እያንዳንዱ ትዕምርት ደግሞ ትርጓሜ የሚያገኘው በበቀለበት ባህል የምግባርና የትውፊት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ ይገልጻሉ (Bell 1997:93)። በተጨማሪም ሥርዓተ ክዋኔ በአብዛኛው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የማሸጋገር ፋይዳ እንዳለውና ፋይዳውም የሚገለጸው በሽግግሩ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ሰፊውን የሥርዓተ ክዋኔ ሂደትና ማህበራዊ መስተጋብሩን ጭምር በመመርመርና በመግለጽ መሆኑን ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል ሥርዓተ ክዋኔ እምነቶችን፣ ትዕምርታዊ የሆኑ መግባቢያዎችን፣ ማህበረሰባዊ የሆኑ ንድፈሃሳቦች እና ሌሎችንም ማህበራዊ ትዕምርቶችን የሚያስተላልፍ የመግባቢያ መንገድ መሆኑም ይገለጻል (Salamone 2004:5)። በተጨማሪም ሥርዓተ ክዋኔዎች አንዳንድ ሁነቶች ከማህበራዊ ፍችዎችና ከትዕምርታዊ ድርጊቶች ጋር ተጣምረው የሚገለጡባቸው በመሆናቸው ሥርዓተ ክዋኔ

ማህበራዊ ወይም ግለሰባዊ ፋይዳ ሊኖረው እንደሚችልም ገልጸዋል። በሌላ በኩል ማህበራዊ የሆነውን ሥርዓተ ክዋኔ ግለሰቦች የሚፈጽሙት ለራሳቸው ግላዊ ፋይዳ ቢሆንም ግለሰቡም ሆነ ማህበረሰቡ የሚረዳው ሥርዓተ ክዋኔውን እየከወኑት መሆኑን ነው የሚሉም አሉ (Myrvold 2007:19)። ስለዚህ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሲጠኑ የሚከወኑበትን ማህበረሰብና የሚጠናውን ጉዳይ መረዳት እንዲቻል የከዋኞቹን ማንነትና የክዋኔውን ምክንያት መረዳት ወሳኝ ነው ብለዋል። በዚህ ጥናትም የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ሲከወኑ የታዩ የጋራ ትዕምርቶችን ለመተንተን፣ ያላቸውን ትስስር ለመረዳት በክዋኔዎች አውድ ውስጥ በመገኘት ሁኔታዎችን ማጤን ተችሏል።

### 3.2. የሥርዓተ ክዋኔ ዓይነቶች

ሥርዓተ ክዋኔዎች በተለያየ ምክንያትና ለተለያየ አላማ እንደሚከወኑ ይገለጻል። ይህም ሥርዓተ ክዋኔዎች የተለያዩ እንዲሆኑ አድርጓል። በዋናነት በማህበረሰቡ ዘንድ ጥንዶች ጋብቻ ሲፈጽሙ፣ ልጆች ለአቅመ አዳም/ሔዋን ሲደርሱ፣ ሰዎችን ለአዳዲስ ደረጃዎችና ሁኔታዎች ለማዘጋጀት፣ ወዘተ. እንዲሁም እንደ ሞት፣ ጉዳት፣ ፍርሃት እና ችግር ያሉ መጥፎ የሕይወት ዘመን አጋጣሚዎች እንዳይከሰቱ፤ ከተከሰቱም ከሚያስከትሏቸው ቀውሶች ለማገገም፣ ጠባቂ ተብለው ለሚታመኑ መናፍስት ጥያቄ፣ ተማጽኖና መስዋዕት ለማቅረብ ሥርዓተ ክዋኔዎች እንደሚፈጸሙ ምሁራን ይገልጻሉ (Salamone 2004:5)። እንዲሁም በማህበረሰቡ ግጭት ሲፈጠር፣ ዝናብ ሲጠፋ፣ ድንገተኛ ሞት ሲደጋገም፣ ህመምና ስቃይ ሲፈራረቅ፣ ባጠቃላይ ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ሲናጉ፣ ሰዎች ሥርዓተ ክዋኔዎችን በመከወን የሚያምኗቸውንና የሚያመልኳቸውን መናፍስት ጥበቃና ከለላ፣ ጤንነትና ደስታ እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ።

Van Gennep ከላይ የተገለጹትን ግላዊ፣ ማህበራዊና ተፈጥሯዊ ቀውሶችን እና የተለያዩ የሰው ልጆች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን በማጠቃለል ሥርዓተ ክዋኔዎችን የደረጃ፣ የቦታ፣ የሁኔታና የጊዜ ሽግግር ሥርዓቶች በማለት በአራት መድበዋቸዋል (Van Gennep 1960:192)። በሌላ በኩል ሥርዓተ ክዋኔዎች ከሚከወኑባቸው አላማዎችና ምክንያቶች በመነሳት ዓመታዊ፣ የሕይወት ሽግግሮች እና የአደጋ ጊዜ በማለት በሶስት ይከፍሏቸዋል (Salamone 2004:576)። ሌሎችም እንዲሁ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ መስዋዕት ማቅረቢያ፣ ጾምን ተከትለው የሚከበሩ እና ፖለቲካዊ ክዋኔዎችን በመጨመር የሥርዓተ ክዋኔ ዓይነቶችን ወደ ስድስት ያደርሷቸዋል (Bell 1997:94-135)። የዚህ ጥናት ትኩረት ግን የሰው ልጅ የህይወት ሽግግር ሥርዓቶች ናቸው።

### 3.3. የሕይወት ሽግግሮች ምንነት

የሕይወት ሽግግሮችን ምንነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ሀሳብ ሰጥተዋል። የሕይወት ሽግግሮች አንድን ግለሰብ (ባለጉዳይ) ከአንድ ግላዊና ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ የሚያሸጋግሩ ሁነቶች መሆናቸውን (Bell 1997:95) እና (Salamone 2004:311) ይገልጻሉ። ከዚህ በማያያዝ

የሕይወት ሽግግሮች የታወቀ መዋቅርን ለመጋራትና ማህበራዊ እሴቶችን ለማስቀጠል ጠቃሚ እሴቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በአፍሪካ ሃይማኖታዊ አውድ የሰው ልጅ የሕይወት ዘመን በአራት ዋና ዋና ወሳኝ ሽግግሮች የተከፋፈለ መሆኑን (Mazama and Asante 2009፡570-577) ገልጸዋል። እነሱም ልደት፣ ለአካለ መጠን (ለአቅመ አዳም/ሔዋን) መድረስ፣ ጋብቻና ሞት ናቸው። እነዚህ አራት ሁነቶች አንድ ሰው ተወልዶ እስከሚሞት ድረስ በሂደት የሚገጥሙትና የሚያልፋቸው የሽግግር ደረጃዎች ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በተወሰኑ ሃይማኖታዊ ምልከታዎች ይገለጻሉ፤ የየራሳቸው ሥነሥርዓቶችና ከበራዎችም እንዳሏቸው አስረድተዋል። በተጨማሪም የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች አንድ ባለጉዳይ የነበረበትን ደረጃ ትቶ ወደቀጣዩ ሲሸጋገር የሚከወኑ መሆናቸውን ገልጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በሕይወት ሽግግሮች ባለጉዳዩ የታጠረበትን አጥር ወይም የተከለለለትን ድንበር አልፎ ወደ ቀጣዩ ማህበራዊ ደረጃ መቀላቀሉን ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ዓላማዎች ያሏቸው ሥርዓተ ክዋኔዎች ይከናወናሉ። ለምሳሌ በወሊድ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ክዋኔዎች ጽንስ የነበረው ወደ ልጅ/ሰው፣ ወላዷን ደግሞ ወደ እናት፤ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎችም ብቸኛ ወይም ላጤ የነበረን/ችን ወደ ባለትዳር፣ እንዲሁም በሞት ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ደግሞ ሕይወት ወደ ሞት (ግዑዝ አስከሬን) መለወጡን ያስተዋውቃሉ፤ ያረጋግጣሉ በማለት ገልጸዋል።

በብዙ ማህበረሰብ ባህል ወሊድ የአንድን ህጻን ወደሚታየው ዓለም በሰላም መቀላቀልን ምክንያት በማድረግ የሚከበር የእንኳን ደህና መጣህ የአቀባበል ስነ ሥርዓት ነው (Salamone 2004፡48)። እኚህ ምሁር ቀጥለውም ሥርዓተ ክዋኔው ከእርግዝና ጀምሮ ሲፈጸም ቢቆይም የወሊድ ጊዜ እናት ጽንሱን የምትገላገልበት በመሆኑ ከፍ ባሉና ተከታታይነት ባላቸው ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይታጀባል። ማህበረሰቡ የአዲሱን ህጻን መወለድ በማስመልከት፣ ውስብስብ እና ድብቅ ጉዳዮችን በመፍታትና በመግለጥ፣ ሃይማኖታዊና አምልኮታዊ ሥርዓተ ክዋኔዎችን በመፈጸም የእናትንና የህጻኑን ደህንነት ይቆጣጠራል ይላሉ።

በሌላ በኩል ወሊድ አንድን አዲስ ኃይል ወደዚች ዓለም ወይም ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀል እንደሆነ ይገለጻል (Mazama and Asante 2009፡576)። የወሊድ ሽግግር ሥርዓቶች ሰውን ሰው የማድረግ ሂደት በእርግዝና ወቅት ተጠናቆ ውጤቱ የሚታይበት በመሆኑ፣ እናትና ልጅ ደህና በመሆናቸው፣ በጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች የሞሸሯቸው ጥንዶች ለፍሬ በመብቃታቸው የሚከወኑ፣ በማህበረሰቡ መካከል ትስስር የመፍጠር አቅማቸውም ከፍተኛ ነው (Grims 1943፡71)።

በብዙ የአፍሪካ ባህሎች በሰው ልጅ የሕይወት ዘመን ከወሊድ ቀጥሎ የሚጠበቀው ለአቅመ አዳም/ሔዋን መድረስ ሲሆን እሱን ተከትሎ የሚካሄደው ጋብቻ መሆኑ ይገለጻል። ከሌሎች የሕይወት ዘመን ሁነቶች አንጻር ሲታይም ሞቅ ደመቅ ባለ ሥርዓተ ክዋኔ ይታጀባል (Salamone 2004፡230)። በብዛት የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔ በሙዚቃና በዳንስ፣ በምግብና በመጠጥ የታጀበ የደስታ መግለጫ አጋጣሚ ተደርጎ እንደሚታይ እኚህ ምሁር አያይዘው ገልጸዋል። በአጠቃላይ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔ ልጆች የልጅነት ጊዜያቸው አብቅቶ ለአካለ መጠን መድረሳቸውን የሚያበስር ወሳኝ የሕይወት ሽግግር ነው።

የሰው ልጅ ተወልዶ፣ በዓለም የኖረውን ያህል ኑሮ በመጨረሻ ሕይወቱ የሚያበቃው በሞት ነው። ሞትን ዕረፍት፣ ኅልፈት፣ መለየት ብለው አለቃ ደስታ ተክለወልድ (1962 ዓ.ም፡756) ይገልጹታል። በብዙ የአፍሪካ ሚቶች፣ ሞት አንድ ሰው በፈጣሪ ጥሪ ወደ ሌላው ዘላለማዊ ዓለም የሚቀላቀልበት ሁነት ነው ተብሎ ይገለጻል። ለአብነት ያህል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ መሰረት ሞት የነፍስና የሥጋ መለያየት መሆኑ ይገለጻል። ነፍስና ሥጋ በትንሣኤ አንድ ሆነው እንደሚነሱ፤ ክርስቶስ በሥጋ ወደ መቃብር፣ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በዚያ የነበሩትን ከነፍስ ሞት ከመከራ ነጻ አወጣቸው። ለሰው ልጅ ከሞት በኋላ ሕይወት ከመቃብር ባሻገር ትንሣኤ መኖሩን አሳየ። በመሆኑም ክርስቶስ ሞቶ ከተነሳ በኋላ ሞት ኃይሉን አጥቷል። ሰውን ወደ ሕይወት፣ ወደ ገነት፣ ወደ መንግስተ ሰማያት፣ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ መሆኑ በዮሐ. ፩፥፳፬ እና በሮሜ. ፰፥፴፩ ተገልጿል።

በሌላ በኩል አንዳንድ ምሁራን እንደሚገለጹት የሕይወት ሽግግሮች በሶስት ቁልፍ ሀሳቦች ላይ የተመሰረቱ ናቸው (Grimes 1943፡73)። የሕይወት ሽግግሮች ከሰው ሕይወት ጋር የተሳሰሩ መሆናቸው፣ የደረጃ ለውጥና ሽግግር ማድረጊያና በሥርዓተ ክዋኔ የታጀቡ መሆናቸው ናቸው። በተጨማሪም በጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ በሕይወት ሽግግሮች ወቅት የሃይማኖት አባቶች፣ መድኃኒት አዋቂዎች የደህንነት መጠበቂያ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ስለሚፈጽሙ በሽግግሩ አዲስ ደረጃ ላይ ያለን ባለጉዳይ በማጠንከር እና በመጠበቅ በኩል ቀላል የማይባል አዎንታዊ ሚናን ይጫወታሉ።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት ባለጉዳይ የነበረበትን ደረጃ አስትተው ለሚቀጥለው የሚያዘጋጁ፣ የሚያሸጋግሩና ወደቀጣዩ ደረጃ የሚያደርሱ (የሚለውጡ) ሁነቶች ናቸው። በመሆኑም ሥርዓተ ክዋኔዎቻቸው ላይ ተደጋግመው የሚገለጡና የሚታዩ የጋራ ትዕምርቶች አሉ። ይህ ጥናትም እነዚህን መመርመርና መተንተን ላይ አተኩሯል።

### 3.4. በሕይወት ሽግግሮች የሚታዩ ትዕምርቶች ምንነት

ትዕምርት ማለት የማህበረሰብ ስምምነታዊ ምልክቶች ሲሆኑ ትርጉም የሚያስገኙት ወጥነት ባለው የጥራት መስፈርት ሳይሆን በማህበረሰቡ ስምምነት መሰረት ነው ሲሉ (Buchler 1939፡208) ገልጸዋል። በተጨማሪም ትዕምርት ማንኛውም ሰው ሰራሽ ወይም ስምምነታዊ ምልክት መሆኑን (Gallie 1952፡116–117) ገልጸዋል። እንዲሁም ትዕምርት ምልክት ሲሆን በምልክቱ እና በተወካዩ ቁስ፣ ሀሳብ፣ ሁኔታ መካከል ያለ ማህበረሰባዊ ስምምነት ወይም በህገ ደንብ የጸና ዝምድና ነው ነው ያሉት (Atkin 2016፡300) ናቸው።

ስነ ማህበረሰባውያን እንደሚሉት ጽንሰ ሀሳቡ መስራች ጆርጅ ኸርበርት ሚድ (George Herbert Mead) መሆናቸውንና በሚከተሉት ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ያነጣጠሩ እንደሆኑ ይገለጻል። የመጀመሪያው የሰዎች ድርጊት የሚገለጸው ሰዎች በተወከሉባቸው ትርጓሜዎች መሰረት መሆኑን፤ የሰዎች ወይም የነገሮች ትርጉም የሚነሳው/ የሚመነጨው አንዱ ከሌላው ጋር ባለው ማህበራዊ መስተጋብር አማካኝነት መሆኑን እንዲሁም ሰዎች ለሰዎችና ለነገሮች ትርጉም የሚያዋቅሩት ከዓለም ጋር ባላቸው ውስጣዊ ግንኙነት መሆኑን በመሰረተ ሀሳብነት የሚጠቅሷቸው ጉዳዮች ናቸው።

የትዕምርት ምንነት በዚህ መልኩ መሰረቱ ይዋቀር እንጅ የኋላ ኋላ በማክስ ዌበር (Max Weber) ማህበራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (social action theory) ተጽዕኖ ስር መውደቁ አልቀረም። ማክስ ዌበር ማህበረሰብ የሰዎች የእንቅስቃሴ ውጤት ወይም ምርት መሆኑን እና ለዚህም አንድን ማህበረሰብ ለማጥናትና ለመተንተን ማህበረሰባዊ ድርጊቶች ዋና ዋና ትኩረቶች ሊሆኑ እንደሚገባቸው ያምናሉ። ይህንንም ለማጤን ትዕምርታዊ መስተጋብር (Symbolic Interactionism) እንደ መረጃ መተንተኛ ተግባዊ መደረጉን ቀጠለ።

ምሁራን እንደሚገልጹት አንድ ሰው ለመኖር አምስት ነገሮች ሊሟሉለት ይገባል። እነሱም ምግብ፣ መጠለያ (ምጣኔ ሀብት)፣ ማህበራዊ ደንብ፣ ትምህርት፣ እና ፖለቲካዊ ተቋማት ሲሆኑ እነሱን ለማግኘት በባህሉ ውስጥ የሚተገበሩ ትዕምርታዊ ሥርዓቶች (እንደ ሃይማኖት፣ እምነት እና እሴቶች) ሚናቸውን ይወጣሉ። እነዚህም የባህል ልዩ ልዩ ትዕምርቶች በሥርዓተ ክዋኔዎች ይተላለፋሉ። ትዕምርቶች አንድን እውቀት ወይም ደንብ መግለጫ መሳሪያ ወይም የተግባቦት መንገድ መሆናቸው ይገለጻል (Firth 1973)። በተጨማሪም ትዕምርት የሰው ልጅ ባህሪን ወደ ጽንሰ ሀሳብ በማሳደግ ሂደት በሰዎች ልምድና እውቀት ስብስብ ነው። ትዕምርቶች የጋራ ማህበራዊ ባህሪዎች የፍች መነሻ ናቸው። የሰው ልጅ ከዓለም ጋር ከሚያደርገው መስተጋብር ፍች በማውጣትና በመተርጎም ያስማማሉ። ትዕምርታዊ መስተጋብሮችም በሚከተሉት መሰረታዊ መመሪያዎች ይዳብራሉ። ሰዎች ለትዕምርቶች ትርጉም የሚሰጡት በራሳቸው አተረጓጎም እንጅ በህገ ደንብ አይደለም። የትዕምርቶች ፍች ከማህበራዊ መስተጋብር ሂደት ይነሳል። ከዚያም ሰዎች በሚያጋጥሟቸው በርካታ ክስተቶች ውስጥ እያደገ፣ እየተሻሻለ እና እየዳበረ ይሄዳል።

የትዕምርቶች ፍች ቋሚ ሳይሆን በልምድ የራስን ማንነት እና የእኛነትን ብያኔ በመጨመር ተደጋግሞ የሚከለስ መሆኑን (Gray 2004፡15-21) ገልጸዋል። በተጨማሪም ትዕምርታዊ መስተጋብር ማኅበረሰብንና ዓለምን ለመረዳትና ለመግለጽ የሚጥር አተያይ ሲሆን በቀጥታ ከማህበረሰብ ቋንቋ፣ ተግባቦት፣ የእርስበርስ ግንኙነት የሚነሳ እና ተመልሶ ወደ ማህበረሰቡ አረዳድ፣ አመለካከት እና እሴት የሚገባ ነው ሲሉ (Crotty 1998፡8) ጨምረው ገልጸዋል። ይህ ጥናትም በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች አከባበር ወቅት የሚገለጡ የጋራ ትዕምርቶችን የማህበረሰብን እውቀትና ልምድ ይዞ መመርመርና መተርጎም ላይ ያተኮረ ነው።

ይህንን ሀሳብ በመጋራት ትዕምርቶች ከማህበረሰቡ ሂደት ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው፣ ከሚፈጸሙባቸው ጊዜዎችና ከሁነቶች ቅደምተከተል ለይቶ መተንተን አይቻልም (Turner 1974፡ 20)። ከዚህ መሰረተ ሀሳብ በመነሳት የሥርዓተ ክዋኔ ትዕምርቶች በማህበራዊ ድርጊቶች ላይ የራሳቸውን አሻራ ያሳርፋሉ። እንደ Firth (1971) ገለጻ ትዕምርቶች አቅም ያላቸው የመረጃ አህዶች መጋዘን ሲሆኑ አስፈላጊነታቸውም ሥርዓተ ክዋኔን ከነአውዱ ለመረዳት ማስቻላቸው ነው።

## 4. የተጠኘ ማህበረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

ይህ ጥናት የተካሄደው በጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ ላይ ነው። ጃቢ ጠህናን ወረዳ በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር ከሚተዳደሩ አስራ አንድ ዞኖች ውስጥ አንዱ በሆነው በምዕራብ ጎጃም ዞን

ውስጥ ይገኛል። ወረዳው ሰላሳ ስምንት የገጠርና ሶስት የከተማ በድምሩ አርባ አንድ ቀበሌዎችን የያዘ ሲሆን፣ በሰሜን ቋሪትና ሰከላ፣ በምስራቅ ደምበጫ እና ደጋ ዳሞት፣ በምዕራብ ቡሬ፣ በደቡብ ቡሬ እና ደንበጫ ወረዳዎች ያዋስኑታል። ከወረዳው እቅድና ኢኮኖሚ ቢሮ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው የወረዳው አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 277,590 እንደሚሆን ይገመታል። ከዚህም ውስጥ 139,616 ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ 137,974 ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው። አማካይ ዓመታዊ የህዝብ ብዛት ፍጥነቱም 2.8%. ይሆናል። በወረዳው ከሚኖረው ህዝብ 94% ያህሉ ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ላይ ሲሆን በተጓዳኝ እንስሳት በማርባትና ንብ በማነብ ተጨማሪ የገቢ ምንጮችን ይጠቀማል። 6% የሚሆነው ደግሞ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጣሪ በመሆንና በንግድ ስራ የሚተዳደር ነው። የህዝቡን ሃይማኖት ስንመለከት 99 ፐርሰንት ያህሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተከታይ ሲሆን ቀሪው አንድ ፐርሰንቱ የእስልምና፣ የፕሮቴስታንት እና የሌላ ሃይማኖት ተከታይ መሆኑን ከላይ በተጠቀሰው የመረጃ ምንጭ ማረጋገጥ ተችሏል።

የጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ የኔ ብሎ፣ ወዶና ፈቅዶ የሚያከብራቸውና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ እና አሁንም ያሉ የህልውናው ምሰሶዎች የሆኑ መልካም እሴቶች ባለቤት ነው። የጃቢ ጠህናን ሰው ቀዳሚውን የዘር ሀረግ ማክበር፣ ሀገርንና ሃይማኖትን መጠበቅ፣ ነባር ባህልን ማክበር፣ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓት፣ መስጠት፣ ማብላትና ማጠጣትን ማበረታታት፣ ርስትንና ባድማን ማክበር ዋና ዋና የጋራ እሴቶች ናቸው።

በተለያዩ ማህበራዊ አውዶችና አጋጣሚዎች በተካሄደ ምልከታ[6] መረዳት እንደተቻለው፣ የጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ በእድሜ፣ በኑሮ ውጣውረድ፣ በሕይወት ልምድ ቀዳሚ የሆኑ ሰዎችን ማክበር፣ ሀገርንና ሃይማኖትን መውደድ ዋና ዋና እሴቶቹ ናቸው። በሕይወተ ስጋ ያሉም ሆኑ በሞት የተለዩ፤ የግለሰብ፣ የማህበረሰብና የሀገር ባለውለታ የሆኑ ደግ እና ጀግና ሰዎች በየአጋጣሚው ይመሰገናሉ፤ ይወደሳሉ። ቅድመ አያት፣ አያት፣ አባትና እናት ልጅን ወልደው፣ በምግባር አሳድገው ለወግ ለማዕረግ ስላበቁ፣ በማህበረሰባቸው መካከል የተጣላን በማስታረቅ፣ ማህበራዊ ጉዳዮችን በመምራትና በማስተባበር፣ ሀገራቸውን ከጠላት በመጠበቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሰዎች ከተተኪ ትውልድ ብድራት እንዲከፈላቸው ይደረጋል። እንደነዚህ አይነት ይዘቶች ያሏቸው ሀሳቦች በክርስትና፣ በጋብቻና በሞት ሥርዓት ከዋኔዎች ወቅት ተደጋግመው ይገለጻሉ።

ከላይ የቀረበው መረጃ የሚያሳየው ማህበረሰቡ ቀዳሚውን ዘር እየቆጠረ ያመሰግናል፤ እነሱም ሆኑ ልጆቻቸው ሀገራቸውን እንዲወዱ፣ ሃይማኖታቸውን እንዲጠብቁ በአደራ መልክ ይነገራቸዋል። ባጠቃላይ ቀዳሚ ቤተሰብን ማክበር፣ ሀገርን መውደድ እና ሃይማኖትን መጠበቅ ሁሉም የማህበረሰቡ አባል የተስማማባቸው፣ የሚጠብቃቸው እና የሚያስቀጥላቸው እሴቶች ናቸው።

በአንድ የእርቅ ሥነ ሥርዓት ላይ በተካሄደ ምልከታ[7] የጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ሲገባ በአካባቢው ሽማግሌዎች አማካኝነት እርቅ ሲካሄድ፣ ግጭቱ ከተራ ኩርፊያ አልፎ ወደ ስድብ እና ድብድብ ከደረሰ፣ ሽምግሌዎች በመጀመሪያ ሁለቱንም ለየብቻ

---

[6] ይህ ምልከታ የተከናወነው በአንድ በቦታና በጊዜ ውስን በሆነ አውድ ላይ ሳይሆን በዋናነት በመስክ ቆይታ ወቅት ባጋጠሙ ማህበራዊ መስተጋብሮች ላይ የተካሄደ ነው፡፡

[7] ምልከታ፣ 23/05/2012 ዓ.ም፣ ምርጫ ቀበሌ ገበሬ ማህበር፣ ምልከታው የተካደው የእርቅ ሥነ ሥርዓት ላይ ነው፡፡

መክረው፣ ገስጸው እና ተቆጥተው ተራ በተራ “ማረኝ/ማሪኝ/ይማሩኝ” “ይቅር በእንተ እግዚሃር” እንዲባባሉና እንዲታረቁ ያደርጋሉ። በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው ከሁለቱ አንዱ በጣም የበደለ እንደሆነ፣ ተበዳይም ተበድያለሁና አልታረቅም ያለ እንደሁ የደንጊያ ጉልቻ ተሸክሞ ማሩኝ እያለ ይለምናል። ተዚያ በደለኛም በሽማግሌ ቁጣና ወቀሳ ጭምር እርቁን ይቀበላል፤ ጥሎ አይኸድም። አንደኛውን እርቁ እንዲጠና፣ ቂማቸው እንዲሽር ከየቤታቸው እየተሄደ እንጀራ ይበላል፤ ጠላም ይጠጣል። ደሞ በዳይ ጥርስ አውልቆ እግር ሰብሮ እንደሆነ የተበዳይ መገጣገጥ (ካሳ) ሽማግሌ በወሰነ ይከፍላል።[8]

የጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች አብሮ መብላትና መጠጣት መገለጫው ነው። ለሌሎች በመስጠት ውስጥ ደስታን እና እርካታን እንደሚያገኙ መረጃ ሰጭዎች ያስረዳሉ። ይህም በሕይወት ሽግግሮች ወቅት በተለያዩ መገለጫዎች ይታያል። “ደግ የሆነች፣ የምታበላና የምታጠጣ ሴት ምጥ አይጠናባትም”፤ “በሕይወት ዘመኑ ሲያበላ ሲያጠጣ የኖረ ሰው አይኮነንም” ተብሎ ይታመናል። በዋናነት ግን መስጠት፣ ማብላትና ማጠጣት የማንነት፣ የማህበራዊ ደረጃ መገለጫ በመሆኑ የማህበረሰቡ አባል የሕይወት ሽግግር ሲያደርግ ከፍ ያለ ድግስ ይደገሳል። በመስጠት ደስታ እንደሚገኝም ይገለጻል። “የወለዱትን ሲስሙለት፣ የሰጡትን ሲበሉለት ደስ ይላል::” እየተባለ ክርስትና፣ ሰርግ፣ ማህበር፣ ሰንበቴ፣ ተዝካር እየደገሰ “አፈር ስሆን”፣ “እንክት ስል”፣ “በሞቴ” በማለት የብሉልኝ ልመና የተለመደ ነው። በምርቃታቸውም “ለሰጭ ይስጠው ለንፉግ ልብ ይስጠው፣ ሁልጊዜ ስጡ፣ ከመስጠት አይለያችሁ፣ ምትሰጡት አትጡ፤ እንጀራህን ሰፋ ያርገው፣ አሁንም ትልቅ እንጀራ ይስጥህ፣ ያያትህን የቅድመ አያትህን እንጀራ ይስጥህ፣ ሰፊ እንጀራ ሰፊ ሀብት ይስጣቸው፣ ቦታውን የሰው አይስጥብህ፣ እንጀራውን ከዚህ ቤት አያውጣው እየተባለ ይመረቃል ::”[9]

ከአቶ እንዳለው ውብቴ[10] ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው የጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ አብሮነቱን ለማስቀጠል የሚጠቀምባቸው የተለያዩ የዝምድና መፍጠሪያና ማጠንከሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማል። የተለመዱ የዝምድና መፍጠሪያ መንገዶች ጋብቻ፣ አበልጅነት፣ ጡት መጥባት፣ የንስኃ ልጅ/ አባት በማድረግ፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን እየደገሱ በመጠራራት፣ ልዩ ልዩ ዓላማ ያላቸው ማህበራትን በመመስረት (የስራ፣ የጽዋ፣ የዘመድ ማህበራት፣ ወዘተ.) መሆናቸውን አስረድተዋል። በእነዚህ ብልሃቶችም የስጋ ዝምድና ያለው ግንኙነቱን ሲያጠነክር (ሲያድስ) ባዕድ የነበረው ደግሞ ዝምድና የሚፈጥርባቸው መንገዶች መሆናቸውን ጨምረው ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ መስጠትን ያበረታታል፤ ያወድሳል፤ በአንጻሩ ክፉትን እና ስግብግብነትን ያወግዛል፤ የአያት ቅድመ አያቱን ርስትና ባድማ ያከብራል፤ ይጠብቃል፤

---

[8]ቃለ መጠይቅ፣ አቶ በላቸው ታደሰ፣ በምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ገበሬ ማህበር የሚኖሩ የሀገር ሽማግሌ፣ በ23/05/2012 ዓ.ም. የተካሄደ፡፡

[9] ምልከታ፣ 07/05/2012 ዓ.ም.፣ ዱምሪ ኪዳነምህረት ቀበሌ በተከናወነ ሰርግ ላይ የተካሄደ ነው፡፡

[10] ቃለ መጠይቅ፣ አቶ እንዳለው ውብቴ፣ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ፣ የሀገር ሽማግሌ ባህል እና ታሪክ አዋቂ፣ በቀን 12/06/2012 ዓ.ም. የተካሄደ ነው፡፡

ያስታውሳል፤ ከዓለማዊው ሕይወት ባልተናነሰ ከሞት በኋላ ላለው ዘላለማዊ ሕይወት አብዝቶ ይጨነቃል፤ ያመቻቻል፤ እንዲሁም የሰጋም ሆነ የመንፈስ መለየትን በድምቀት ያከብራል። የመለየት ጊዜ ዋናው ሽግግር የሚካሄድበት ወቅት በመሆኑ ባለጉዳይን ወደቀጣዩ ደረጃ የሚያደርስ፣ ለለውጥ የሚያጋልጥ ወሳኝ ጊዜ በመሆኑ በሥርዓተ ክዋኔዎች እየታጀበ ይከበራል።

## 5. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶችን ከማህበረሰቡ ባህል፣ እምነትና እውቀት በመውሰድ ግላዊና ማህበራዊ ሕይወቱን እንዲሁም አተያዩን የተነተነ፣ የገለጸና የተረጎመ ነው። ለዚህም ቀዳማይ መረጃዎች በምልከታና ጥልቅ በሆነ ቃለ መጠይቅ ዘዴዎች ተሰብስበዋል። በዚህ ጥናት ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ሲውል የጥናቱን ዓላማ ያገናዘበ መሆኑን፣ ተስማሚነቱና ተገቢነቱ ተመዝኗል። ከምልከታ ቀጥሎ ቃለ መጠይቅ አስፈላጊ መረጃ አስገኝቷል። ከሀገር ሽምግሌዎች ጋር በተካሄደ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ አማካኝነት በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች (ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት) ሲከወኑ የታዩ ተመሳሳይነት ያላቸውና የጋራ የሆኑ ቁሶች፣ ሁነቶች፣ አገላለጾች፣ ቁጥሮች፣ ወዘተ. ትዕምርትነታቸው የምን እንደሆነ ተደጋግመው የመምጣታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ መረዳት ተችሏል። ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ የሚገልጹና የሚያብራሩ ጽንሰ ሀሳቦችንና ንድፈ ሀሳቦችን፣ ተያያዥ የሆኑ ቀደምት ጥናቶችን እንዲሁም የጥናቱን አካባቢ የሚያስተዋውቁ መረጃዎችን ማግኘት ተችሏል።

የዚህን ጥናት ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መረጃዎች ሲሰበሰቡ ከአጠቃላይ ተጠኝ ማህበረሰቡ ውስጥ ወካይ ሊሆን የሚችል ናሙና አላማ ተኮር በሆነ ስልት በወረዳው ካሉ አርባ አንድ ቀበሌዎች መካከል የዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁለት ቀበሌዎች ተመርጠዋል። መረጃ ለመስጠት ከተመረጡ ሰላሳ አምስት ሰዎች ውስጥ ስምንቱን ቁልፍ መረጃ ሰጪ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የተተነተኑት በይዘት ሲሆን አቀራረቡም አውድን መሰረት ያደረገ የገለጻና የትርጎማ ስልትን የተከተለ ነው።

ቃለ መጠይቁ እና ምልከታው ሲከናወን ለተሳታፊዎች የጥናቱን ዓላማና ጥቅም በማስረዳትና ፈቃዳቸውን በማግኘት፣ ለመረጃ ሰጭዎች የጊዜና የሁኔታ ምርጫና ምቾት ቅድሚያ በመስጠት፣ ቀድሞ እነሱ የተስማሙበትን ቀጠሮ በመያዝ፣ በሚመቻቸው ጊዜና ቦታ በመገናኘት ተሰብስቧል። መቅረጸ ድምጽ ለመጠቀም ፈቃደኛ ከሆኑ መረጃ ሰጭዎች መሳሪያውን መጠቀም ተችሏል። በአንጻሩ ድምጻቸው እንዳይቀዳ የፈለጉ መረጃ ሰጭዎችን ሀሳብ ማስታወሻ ደብተር ላይ በመጻፍ ተሰብስቧል። በዚህ መሰረት ምልከታን በመጠቀም የሕይወት ሽግግሮች ሥርዓተ ክዋኔዎች ሲከናወኑ ተደጋግመው የተገለጡ ትዕምርቶች ተሰብስበዋል። እነዚህ ትዕምርቶች ያላቸው ትርጓሜ ተደጋግመው የመምጣታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ የሚያመለክቱ መረጃዎች ደግሞ በቃለ መጠይቅ ዘዴ ተገኝተዋል። በመጨረሻም መረጃዎችን በማደራጀት ሂደትና በትንተና ወቅት የተመራማሪዎች የግል ስሜትና አመለካከት እንዳይንጸባረቅበት ጥንቃቄ ተደርጓል።

## 6. በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የተገለጡ የጋራ ትዕምርቶች ትንተና

በዚህ ክፍል በሕይወት ሽግግሮች (በወሊድ፣ በጋብቻ እና በሞት) ሥርዓተ ከዋኔዎች ወቅት ተደጋግመው የተገለጡ ባህሪያት፣ የጋራ ሀሳቦችና ቁሶች ተተንትነዋል። ቀጥሎም ከነዚህ የጋራ ትዕምርቶች በመነሳት የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ትስስር ምን እንደሚመስል ለማሳየት ተሞክሯል። የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ የሕይወት ሽግግር ሥርዓተ ከዋኔዎች ወቅት ተደጋግመው የታዩ ትዕምርቶች አጋጥመዋል። እነሱም በቁሶች እና በቁጥሮች አማካይነት ተከስተዋል። ከዚህ ቀጥሎ የእነዚህ ትዕምርቶች ትንተና ቀርቧል።

### 6.1. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል/ለውጥ በተሰኙ ሦስት የመዋቅር ደረጃዎች የሚያልፉ መሆናቸው

በሕይወት ሽግግሮች የሚካሄድ ለውጥ አስፈላጊና ተከታታይ በሆኑ ሶስት ደረጃዎች (መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል) አማካኝነት የሚያልፉ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል። ባለጉዳይን ከለመደውና ከቆየበት ሁኔታ ወደ ሌላ አዲስ ደረጃ ያሸጋግራሉ። በወሊድ ሽግግር ህጻኑ ዘጠኝ ወር ከቆየበት ከማህጸን ዓለም ተለይቶ ለዚህ ለሚታየው ዓለም ይጋለጣል። እናትም ከእርግዝና ጊዜዋ ጀምሮ ከአንዳንድ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ትለያለች። እስከ ክርስትና ድረስም ከልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮችና ከቆየችበት የሕይወት ልምድ ትነጠላለች። በወሊድ ሽግግር ውስጥ የእርግዝና እና የአራስነት ጊዜ ለእናት የመነጠል ጊዜ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የምጥ ጊዜ፣ የጥምቀትና የክርስትና ሥርዓት ደግሞ ሌሎች የሽግግር ወቅቶች ናቸው። ከህጻኑ አንጻርም እንዲሁ እስከ ክርስትና ያለው ጊዜ የመነጠል የክርስትናው ስነ ሥርዓት የሽግግር ጊዜ እና ከክርስትናው በኋላ ያለው የቅልቅል ጊዜ ነው ማለት ይቻላል። ከዚያም እናትና ልጅ በአዲስ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ማህበረሰቡን ይቀላቀላሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ እናት ከነፍሰ ጡርነት ወደ እናትነት፤ ጽንስ የነበረውም ወደ ልጅነት ወይም ሰውነት ደረጃ ይደርሳሉ።

የጋብቻ ሽግግርም ሙሽሮች ከመታጨታቸው ጀምሮ እስከ ጫጉላ ግላጭ/ቅልቅል ድረስ ዋናው የሽግግር ወቅት ሲሆን እስከ ሰርጉ እለት ድረስ ያለውን የመነጠል ጊዜ፣ የሰርጉ ስነ ሥርዓት እና የጫጉላ ቤት ቆይታ የሽግግር ጊዜ እንዲሁም የጫጉላ ግላጭ/ ቅልቅል ደግሞ የቅልቅል ጊዜ ነው። ባለጉዳዮች ከብዙ አካላዊና ስነ ልቡናዊ ለውጦች ጋር ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ። በምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ገበሬ ማህበር በተካሄደ ባህላዊ ሰርግ ላይ በተካሄደ ምልከታ[11] የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ሙሽሮች ከሰርጋቸው ጀምሮ እናት አባታቸውን፣ ልጅነትን፣ ድንግልናን፣ ስምን፣ ነጻነትን[12] ወዘተ. አጥተው ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ። ለውጡም በሚያደርጓቸው ጌጣጌጦችም ሆነ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ይገለጻል።

---

[11]ምልከታ፣ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ገበሬ ማህበር በተከናወነ ሰርግ ላይ የተካሄደ፣ ምልከታው የተካሄደበት ቀን 25/05/2012 ዓ.ም

[12]መረጃ ሰጭዎች እንደሚሉት በጃቢ ጠህናን ወረዳ ጋብቻ ለተጋቢዎች ብዙ ነገሮችን አሳጥቶ ብዙ ነገሮችን ይዞ ይመጣል፡፡ ልጆች ከጋብቻ በፊት እንደልብ ከእኩዮቻቸው ጋር ተሯሩጠው መጫወት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር አብሮ መኖር፣ አብሮ መብላት፣ አብሮ መተኛት፣ ባጠቃላይ ህጻናት የሚኖራቸው ነጻነት አላቸው፡፡ በዚሁ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ጋብቻ መፈጸማቸውን ተከትሎ ከነዚህ እንቅስቃሴዎች ሙሉ በሙሉ ይታገዳሉ፡፡ በምትኩ ሥራ መስራት፣ ከማያውቁት ቤተሰብ ጋር መኖር (በተለይ ሴት ሙሽሮች)፣ ከትዳር አጋር ጋር መተኛት፣ እንደ ትልቅ ማስተዋልና መጠንከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የልጆችን አካላዊና ስነልቡናዊ ነጻነታቸውን እንደሚያሳጣቸው የሕይወት ልምዳቸው ያጋሩ መረጃ ሰጭዎች አስረድተዋል፡፡

የሞት ሽግግርም ባለጉዳይን ከመኖር ወደ አለመኖር የሚለውጥ አሉታዊ መልክ ያለው ነው። የእርጅና ጊዜ እንደ መነጠል፣ የሞት ጊዜ ደግሞ እንደ ሽግግር እንዲሁም ከሞት በኋላ ያለው ክንውን ደግሞ የቅልቅል ጊዜ ነው። ከዚህ ሀሳብ በመነሳት መነጠል አንድ የሕይወት ሽግግር ለማድረግ ዝግጅት የማድረጊያ ጊዜ ነው ሊባል ይችላል። ሽግግር ቀድሞ የነበረ ሁኔታ የሚያበቃበትና ለአዳዲስ ሁኔታዎች የሚጋለጥበት ወሳኝ ወቅት ሲሆን ቅልቅል ደግሞ በሽግግር ወቅት የተዋወቁ አዳዲስ ሁኔታዎች ተይዘው የሚቀጥሉበት ነው። በመሆኑም በመነጠልና በቅልቅል ወቅት ያሉ ሁኔታዎች ፈጽሞ የማይተዋወቁ፣ ነገር ግን በሽግግር ጊዜው ድልድይነት የተገናኙ፣ በቅልቅል ጊዜ የሚጠበቅና የማይቀረው ለውጥ የሚገለጥበት ጊዜና ሁኔታ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### 6.2. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች እንደ እሴቶች መገለጫ

የጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ላይ አራት ጉዳዮች ተደጋግመው ይገለጣሉ። የማህበረሰቡ አባል ጥሩ ምግባር እንዲኖረው፣ ወደዚች ዓለም ለመምጣት ምክንያት ሆነው፣ አሳድገው ለቁምነገር እንዲበቃ ያደረጉ ወላጆችን በማክበር ብድራቱን እንዲመልስ በየአጋጣሚው እየተነገረው፣ ከቀደሙት እየተማረ ያድጋል። ይህም አንድ ህጻን ሲወለድ ጀምሮ በክርስትናው ጥሩ ምግባር እንዲኖረው፣ ሰው አክባሪ፣ ጨዋ፣ ምግባሩ የቀና፣ ሃይማኖቱ የጠና እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን ደጋግመው ይገልጻሉ። የማህበረሰቡ አባል የሆነ ሁሉ ከቀደሙ አባቶቹ የተረከበውን የጋራም ሆነ የግል ቦታውን፣ ባድማውን፣ ርስቱን እንዲጠብቅ፣ ከፍ ሲልም ሀገሩን እንዲወድና እንዲያስከብር ይፈለጋል። በመሆኑም "ሀገር አስከባሪ፣ ወንዝ አሳፋሪ" እንዲሆን በተለይም በወንድ ልጅ ክርስትና እና ሰርግ ላይ እንዲሁም በሞቱ ወቅት የእነዚህ ትዕምርቶች ማደሪያ የነበረ መሆኑ ተደጋግሞ ይገለጻል። ሴቶች መልካም ምግባር እንዲኖራቸው በሰርጋቸው "አጥር ቆስቋሽ ነገር አመላላሽ አያድርጋችሁ!" እየተባሉ ይመረቃሉ። በሞት ሽግግርም ሟች የነበረውን መልካም ምግባር፣ ሰው ወዳድነት፣ ስራ ወዳድ፣ ለሌላ መስጠትን፣ ማብላት ማጠጣትን፣ አብሮ መኖርን፣ ሃይማኖትንና እምነትን ቀሪው ትውልድ እንዲያጸና በአደራ መልክ ይነገራል። ይህ የሚያሳየው ምግባር፣ ቀዳሚን ማክበር፣ ሃይማኖትን እና ሀገር መውደድ እንዲሁም መጠበቅ ከእያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል የሚጠበቁ ቁምነገሮችና የህልውናው ማስጠበቂያ ምሰሶዎች መሆናቸውን ነው።

### 6.3. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች እንደ ማህበራዊ መዋቅር መግለጫ፣ ማጠንከሪያና ማስጠበቂያ ሁነት

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ የእርስበርስ መስተጋብር መረዳት እንደተቻለው ጾታ፣ እድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የወሊድ ሁኔታና ስልጣን ማህበራዊ ደረጃን ይወስናሉ። ከሴቶች ይልቅ ወንዶች የተሻለ ደረጃ ያላቸው መሆናቸውን አመላካች እሳቤዎችና ድርጊቶች ይስተዋላሉ። ለአብነት ያህል በቤተሰብ ውስጥ ወንዶች ምግብ ሳይበሉ ሴቶች አለመብላት፣ የተለየና የተመረጠ ጥሩ ነገር ካለ ለወንዶች ማድላት፣ ሳይተኙ አለመተኛት የመሳሰሉ ጉዳዮች ይስተዋላሉ። በእድሜ ትልቅ የሆኑ ሰዎችም እንዲሁ የተሻለ ማህበራዊ ደረጃ አላቸው። ካላገቡ ወይም አግብተው ከፈቱ ሰዎች ይልቅ ያገቡና በትዳር ያሉ የተሻለ ክብር አላቸው። ካልወለዱ ወይም ከማይወልዱ ሰዎች ይልቅ የወለዱ

ተቀባይነት አላቸው። ስልጣን በብዛት ሃይማኖትን መሰረት አድርጎ የሚገለጽ ሃይማኖታዊ ትምህርትን በየደረጃው የተማሩ (ዲያቆን፣ ቄስ፣ መነኩሴ፣ ጳጳስ፣ …)፣ ከጨዋ እና ከሴቶችም ቆራቢዎችና መነኩሴዎች የተሻለ ክብር አላቸው። ይህም በክርስትና፣ በሰርግና በሞት ሥርዓቶች ላይ በሚገለጡ ሥርዓተ ክዋኔዎች በግልጽ ይታያል። በዚህ መሰረት የማህበረሰቡ መዋቅርና ተዋረዳዊ ግንኙነት ተጠብቆ እንዲቀጥል ያደርጋሉ።

## 6.4. የሽግግሩ ዋና ባለጉዳዮች ጥበቃና እንክብካቤ የማይለያቸው መሆናቸው

በሶስቱም የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች (ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት) ሽግግር የሚያደርጉ ባለጉዳዮች ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በወሊድ ወቅት እናት በዋናነት እስከ አስር ቀን፣ ልጅ ክርስትና እስከሚነሳ ድረስ ጥበቃና እንክብካቤ ይደረግላታል። በጋብቻ ሽግግር ወቅት ሙሽሮች በዋናነት እስከ ጫጉላ ግላጭ (ቀደም ሲል እስከ አርባ ቀን አሁን እስከ አምስት ወይም አስር ቀን ድረስ) ጥበቃ እንደሚደረግላቸው በምልከታ[13] የተገኘው መረጃ ያሳያል። አቶ ለገሠ[14] እንዳሉት ከሆነ በሞት ሽግግር ወቅትም እንዲሁ "እንግዲህ ሰው ታሞ ታሞ እየደከመ ሲሄድ እና እንደማይተርፍና በሕይወት እንደማይቆይ ሲገመት ሰው ሁሉ ከያለበት ይሰበሰባል። ከዚያም ነፍስና ስጋው ተለያይተው የሬሳው ግብዓተ መሬት እስከሚፈጸም ድረስ ብቻውን አይተወም፤ ነውር ነው። ቀጥሎም ሀዘንተኞች ቢያንስ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ብቻቸውን አይሆኑም፤ እንክብካቤም ይደረግላቸዋል።" በእነዚህ ወሳኝ የሽግግር ወቅቶችና ሁኔታዎች የሚገኙ ባለጉዳዮች በተለይ የአራስነትና የሙሽርነት ጊዜ በክፉ መንፈስ ሊጠቁ የሚችሉባቸው አውዶች ሲሆኑ ከሞት በኋላ ደግሞ ተጠቂ ወይም ተጋላጭ መሆናቸው ቀርቶ አስጠቂ ወይም አጋላጭ ወደመሆን ይሸጋገራሉ። በሕይወት ያሉ ሰዎች ደህንነት ተጠብቆ እንዲቆይ ሲባል የባለጉዳዮች በአራስነትና በሙሽርነት ጊዜ ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ከሞት በኋላም የአስከሬን ግብዓተ መሬት እስከሚፈጸም ድረስ እንዲሁ ጥበቃ ይደረጋል። አላማውም በሕይወት ያሉትን ለመጠበቅ እንደሆነ ይታመናል።

እነዚህ ወሳኝ የሽግግር ወቅቶች ለክፉ መንፈስ አጋላጭ ስለመሆናቸው ብዙ ገጠመኞች ይነሳሉ። የአራስነት ጊዜ ክፉ መንፈስን ይጠራል ተብሎ ይታመናል። ይህም እናትን ወይም ልጅን አስጠቅቶ ጤናን ወይም ሕይወትን ያሳጣል። በመሆኑም እናቶች ከተገላገሉ ጀምሮ በአራስነት ጊዜያቸው የሚጠብቃቸው ሰው ባይገኝ/ቢቸግር እንኳ ከብርና ከነሐስ የተሰሩ ጌጣጌጦቻቸውን (ብር ቅጥል፣ ድሪ፣ ጠልሰም፣ አምባር፣ ወዘተ.) በአንገታቸው እና በእጃቸው፤ ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎችን (ቢላ፣ ጠበንጃ) በራስጌያቸው፤ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው መጻሕፍትን (መጽሐፍ ቅዱስ፣ የጸሎት መጻሕፍት) በአጠገባቸው ሲያደርጉ ጥበቃ እንደሚያደርጉላቸው ይነገራል። እነዚህ ቁሶችም ክፉ መንፈስ የማይወዳቸው በመሆናቸው ከአካባቢው ያርቃሉ ተብሎ ይታመናል።

የሙሽርነት ወቅትም ለክፉ መንፈስ ያጋልጣል የተባለበትን ምክንያት አቶ ለገሠ ሲያብራሩ ሙሽርነትን "የአበባ ጊዜ እንደማለት ነው።" ሲሉ ይገልጹታል። የሙሽርነት ጊዜ የሚያምሩበትና

---

[13] ምልከታ፣ ዱምሪ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ ቄስ ጺጋ የተባሉ አባወራ ሶስት ልጆቻቸውን ሲድሩ በመገኘት በቀን 07-10/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ

[14] ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ለገሠ እምሩ፣ የምርጫ ቦራቡር ቀበሉ ገበሬ ማህበር ነዋሪ፣ የሀገር ሽማግሌ፣ ታሪክና ባህል አዋቂ፣ በቀን 13/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ

የሚዋቡበት ወቅት በመሆኑ ሰው ለማየት እንደሚጓጓው ሁሉ ክፉ መንፈስም ይፈልጋቸዋል። በዚህም በሙሽርነታቸው ወቅት ብቻ ሳይሆን ከመታጨታቸው ጀምሮ ትኩረትን ይስባሉ ተብሎ ይታመናል። በሞት ወቅትም የሟች ነፍስና ስጋ ከተለያዩ ጀምሮ እስከ ቀብር ድረስ አስከሬኑ ብቻውን እንዲሆን አይተውም፤ ይጠበቃል። ከዚያም ቢያንስ እስከ ሶስት ቀን ሀዘንተኞች አስከሬን በወጣበት ቤት ውስጥ ብቻቸውን እንዲሆኑ አይመከርም። ምክንያቱ ደግሞ ሰው ነፍሱ ከወጣች በኋላ የክፉ መንፈስ ማደሪያ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ያ ክፉ መንፈስም በሕይወት ያሉትን እንዳያጠቃ ግብዓተ መሬት እስከሚፈጸም ድረስ ጥበቃ በማድረግ ለመከላከል ይሞከራል።

በወሊድ እና በጋብቻ ወቅት እራሳቸው ባለጉዳዮች የሚጠበቁት በክፉ መንፈስ እንዳይጠቁ (እንዳይጋለጡ) ሲሆን በሞት ጊዜ አስከሬን የሚጠበቀው ሌሎችን በህይወት ያሉትን ደህንነት ለመጠበቅ ነው። ከዚህም ክፉ መንፈስ የሚያጠቃው ሕይወትን/ነፍስን እንደሆነ በአንጻሩ የሰው ሕይወት ከስጋ ሲለይ ከመጠቃት ይልቅ አስጠቂ ወደመሆን እንደሚሸጋገር እንረዳለን። ጋብቻ፣ ወሊድ፣ እርጅናና ሞት ለክፉ ዐይን አጋላጭ አውዶች መሆናቸውን ዋልተንጉሥ (2007፡158) ጠቁመዋል። በመሆኑም በሕይወት ሽግግሮች ወቅት የሚደረግ የባለጉዳይ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግበት አላማ እንደሁኔታው ቢለያይ ለባለጉዳዮች ደህንነት ሲባል ነው። ይህ ጉዳይ በሶስቱም የህይወት ሽግግሮች ተደጋግሞ በመምጣቱ የጋራ ባህሪ ተደርጎ ተወስዷል።

## 6.5. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች እንደ ማህበራዊ መስተጋብር መግለጫ

የሕይወት ሽግግሮች በባህሪያቸው በማህበረሰቡ ተሳትፎ የሚከበሩ ናቸው። ዋናው ሽግግር የባለጉዳዩ ብቻ ቢሆንም፣ የሽግግሮች ሂደትና የሚያስከትሏቸው ውጤቶች በማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ተሳትፎ የታጀቡ ናቸው። ወሊድ እና ጋብቻ የደስታ፣ ሞት ደግሞ የሀዘን መግለጫ አጋጣሚዎች ናቸው። በጃቢ ጠህናን የግል ደስታም ሆነ ሀዘን የለም። የማህበረሰቡ የጋራ ጉዳዮች በመሆናቸው የሚፈጥሯቸው ስሜቶች ቢለያዩም (ደስታና ሀዘን) በማህበረሰቡ የጋራ ተሳትፎ የሚከበሩ መሆናቸው ግን የጋራ ባህሪያቸው ነው። ለምሳሌ የምጥ ወቅት ወላዷን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡን ሁሉ ያስጨንቃል። በሰላም ስትገላገልም ሁሉም ሰው ደስታውን በእልልታና በመሳሳም ይገልጻል።

በጋብቻ ወቅትም እንዲሁ ሙሽሮች ወይም የሙሽሮች ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆኑ፣ ያሳደጋቸው ጎረቤት፣ በአካል የማያውቃቸው ወዳጅ ዘመድ ጭምር ዘፍኖ፣ ደግሶ ይድራቸዋል። በሁኔታውም ይደሰታል። የክርስትና ሥነሥርዓትም የህጻኑን ወደ ማህበረሰቡ መቀላቀል የሚያውጅ በመሆኑ የጋራ ደስታ ነው። በመሆኑም በክርስትና እና በጋብቻ ማህበረሰቡ "መጥታችሁ ልጃችሁን መርቁ!" እየተባለ የደስታው ተካፋይ እንዲሆን ይጠራል። ይህም አዲስ የተወለደው ልጅም ሆነ የተሞሸሩ ሙሽሮች የወላጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ የማህበረሰቡ ጭምር መሆናቸውን፣ ለማህበረሰቡ ቁጥር መጨመር፣ መስፋፋት፣ መብዛት አስተዋጽዖ የሚያበረክቱ በመሆናቸው በጋራና በደስታ ስሜት ያከብራቸዋል።

በአንጻሩ ሞት አብሮ የኖረን ሰው የሚቀንስ፣ የሟች ቤተሰብንም ሆነ ማህበረሰብን የሚጎዳ፣ የሚያሳንስ በመሆኑ አሳዛኝና አስደንጋጭ ሁነት ነው። በመሆኑም ጉዳቱ በቀላሉ የሚሽር አይደለም። ለዚህም ማህበረሰቡ የደረሰውን ጉዳት በመረዳዳትና በአብሮነት ያልፈዋል። ሟችን የሚያውቅም

ሆነ የማያውቅ የማህበረሰቡ አባል አልቅሶ ይቀብራል፤ ሀዘንተኞችን ያጽናናል። ከቤተሰብና ከወዳጅ ዘመድ በተጨማሪ እድርተኛ እና ማህበርተኛ ሟችን አልቅሶ በመቅበር፣ ለቀስተኛን በማስተናገድ፣ ቤተሰብን በማጽናናት እና መታሰቢያውን በማክበር የተለየ ኃላፊነት አለበት። በማዘን፣ በማስተዛዘን፣ በማጽናናት፣ በማገዝ አብሮነቱ ያልተለየው ማህበረሰብም በአርባ ቀን መታሰቢያ “መጥታችሁ ስንላቀስ እንድናመሽ!” እየተባለ የሀዘን መደምደሚያ የሆነውን የአርባ ቀን መታሰቢያ በጋራ እንዲያሳልፉ ይጠራሉ። የተጠራው ሰው አቅሙ የፈቀደውን (እንጀራ፣ አረቄ፣ ጠላ፣ ገንዘብ) ለሀዘንተኞች በመስጠት እንዲሁም በሀሳብና በጉልበት አብሮነቱን ይገልጻል። ወሊድና ጋብቻ አዎንታዊ ትርጉም ያላቸው የሕይወት ትዕምርቶች ሲሆኑ አዲስ ሰውን ወደ ማህበረሰቡ የሚጨምሩ በመሆናቸው አስደሳች ናቸው። ሞት ደግሞ የአጉዳይነትና የአሳናሽነት ትዕምርት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት በትልቁ ማህበረሰብ ውስጥ የግለሰብን ዋጋ የምንረዳባቸው ክስተቶች ናቸው። እነሱን ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎችም የማህበረሰቡ የእርስበርስ ትስስርና አብሮነት የሚገለጥባቸው ሁነቶች መሆናቸውን እንረዳለን።

## 6.6. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የሰላምና የእርቅ ማወጃ መሆናቸው

የሕይወት ሽግግሮች የሰላም ማወጃ ወይም የእርቅ መፈጸሚያ አጋጣሚዎች ናቸው። ማህበረሰቡ በተለያየ ምክንያት ግጭት ውስጥ ሊገባ ይችላል። አቶ ለገሠ እንደተናገሩት ከሆነ በሕይወት ሽግግሮች (በወሊድ፣ በጋብቻ እና በሞት) ወቅት የተጣላ ይታረቃል። በወሊድ ወቅት ወላዲ ምጥ ከጠናባት ያስቀየመችው ወይም የተቀየመችው ሰው ካለ ተጠርቶ “ማሩኝ” እንድትለው ይደረጋል። በጊዜውና በሁኔታው የተገኙ ሴቶች መቀነታቸውን፣ ወንዶች ደግሞ ቀበቷቸውን ይፈታሉ። ምክንያቱም ከወላዲ ጋር የነበረን ቂም እና ጥላቻ ከመሻር ጋር እንደሚያያዝ መልዓከ ጥበብ ስሜነህ አበበ[15] ይገልጻሉ። የበደሉትንም ሆነ የበደላቸውን ሰው ይቅርታ መጠየቅ ምጧ እንዲቀል ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።

መልዓከ ጥበብ ቀጥለውም በጋብቻ ወቅትም ሰርጉ እየተቃረበ ሲሄድ በእለት ተዕለት ሕይወታቸው የተጣሉት፣ ያስቀየሙት እና ያስቀየማቸው ሰው ካለ ገና በዋዜማ የከብት እርዱ ከመከናወኑ በፊት እርቅ ይፈጸማል።[16] ሰላም ይወርዳል። እርቁም በታረደው ከብት ደም ይጠናል። ከዚያም ቂማቸውን በመርሳት ወይም ነገሩን በመተው መገናኘት ይጀምራሉ። በሰርጉ ስነ ሥርዓትም አብረው ይሳተፋሉ። ይህ እርቅ ለሰርጉ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ መስተጋብራቸው ሁሉ ሰላማዊ እንዲሆን ያደርጋል። ጋብቻ በደም የሚፈላለጉ ሰዎችን ጭምር አስታርቆ ያዛምዳል ይላሉ።

[15] ቃለ መጠይቅ፣ መልዓከ ጥበብ ስሜነህ አበበ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን የስብከተ ወንጌል ሃላፊ፣ የሀገር ሽማግሌ፣ ታሪክና ባህል አዋቂ፣ በቀን 03/06/2012 ዓ.ም የተካሄደ

[16] ሰርገኞች ወይም ደጋሾች የተጣሉት ሰው ካለ የከብት እርድ ከመፈጸሙ በፊት ሥርዓተ እርቁ ይፈጸማል፡፡ ምክንያቱም የከብት እርዱ ሰርጉ በይፋ መጀመሩን የሚያበስር በመሆኑ ቀድሞ ሰላም ማውረድ ይገባል ከሚል እሳቤ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ እርቁ በእርዱ ደም እንደሚጸናም ይገለጻል፡፡ እርዱን ተከትሎ በጋራ መብላትና መጠጣት መጎራረስ፣ መሳቅ መጫወት የሚቀጥል የሚከናወን በመሆኑ እርቁንን የበለጠ ያጸናሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚህም በሰርግ ብቻ ሳይሆን የሰው ነፍስ የጠፋባቸው እና ከበድ ያሉ ግጭቶችን ለመፍታት በሚደረጉ የሽምግልና እና የእርቅ ሥነ ሥርዓቶች ላይ እርቁን ለማጽናት እርድ መፈጸም የተለመደ ነው፡፡

በመጨረሻም መልዓከ ጥበብ ሞትም እንዲሁ ለቀሪው ማህበረሰብ የሰላም ማውረጃ ሁነት መሆኑን አክለዋል። ይህም ሲባል ሟች በተለይ በእድሜ የገፋ ከሆነ በእርጅና ጊዜው ከፈጣሪና ከሰው ጋር እርቅ ይፈጽማል። ንስኃ በመግባት፣ በመጾም፣ በመጸለይ፣ ምጽዋት በመስጠት፣ የተጣላን በመታረቅ፣ ዓለምን ንቆ በመሰደድ፣ ስጋን በማድከም፣ ስጋወ ደሙን በመቀበል፣ ሥርዓተ ምንኩስና በመፈጸም ከፈጣሪ ጋር እርቅ በመፈጸም መልካም ግንኙነት የሚጀምርባቸው ተግባራት ናቸው ይላሉ። ከዚያም ሲታመምና ሲደክም አውቆም ይሁን ሳያውቅ ያስቀየመው ሰው ካለ ተጠርቶ ይቅር እንዲባባሉ ይደረጋል። ከሞት በኋላም በዕለቱ ሥርዓተ ፍትኃት ተደርጎለት፣ ከዕለት እስከ ዓመት ድረስ በተለያዩ ቀናት የሚከናወኑለት የመታሰቢያ ሥርዓቶች እንዲሁ ሟችን ከፈጣሪ ጋር ያስታርቃሉ ይላሉ። ቀድሞ እነዚህ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ያልፈቷቸው ችግሮች፣ የቋጠሯቸው ቂም በቀሎች ቢኖሩ እንኳ በሞት ጊዜ ይሻራሉ። ነገሩን በሙተው ወደ ሀዘንተኞች ቤት ይገባሉ፤ ሀዘኑም ሀዘናቸው ይሆናል።

## 6.7. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች መለየት/ መነጠል የሚከበርባቸው ሁነቶች መሆናቸው

የሕይወት ሽግግሮች በዋናነት መለየትን የሚያውጁና የሚያከብሩ ናቸው። መለየት በወሊድ፣ በጋብቻ እና በሞት ጊዜ የሚገለጥ የጋራ ትዕምርት ነው። የሰው ልጅ በወሊድ ከእናቱ ማህፀን፣ በጋብቻ ከቤተሰብ፣ ከአካባቢና እንዲሁም ከራሱ ማንነት ጭምር፣ በሞት ከስጋ ሕይወት እና ከዓለም ይለያል። በባለጉዳዩ ቀዳሚና ተከታይ የሕይወት ሁኔታ መካከል ያለው ልዩነትም ፍጹም ተቃርኗዊ ነው። ከአንድ ደረጃ ወደቀጣዩ ለመሸጋገር መለየት የግድ ይሆናል። በወሊድ፣ በጋብቻና በሞት ምክንያት የሚያጋጥሙ መለየቶች ጠበቅ ያሉና አስጊ[17] በመሆናቸው በቀላሉ የሚታለፉ አይደሉም። በመሆኑም እንደ ሽግግሮቹ ዓይነት ማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎችን[18] በመፈጸም ያከብራቸዋል።

---

[17] የሕይወት ሽግግሮች (ወሊድ፣ ጋብቻ እና ሞት) የደረጃ ለውጥ ለማካሄድ የሚያስችሉ የሽግግር (Liminal) ወቅቶች ናቸው (Turner, 1967)፡፡ ወሊድ ለሕይወት፤ ሞት ለዘላለማዊው ዓለም፤ እንዲሁም ጋብቻ ለአዲስ ፍሬ የሚያበቁ ወሳኝ የሽግግር ሁነቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት ሽግግር በባህሪው በአንድ በኩል አሙለጭላጭ/ አንሸራታች፤ በሌላ በኩል አቅም የሚያመነጭ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ይወሰዳል ይላሉ፡፡ በሽግግር ወቅት ያለ ባለጉዳይን ሌሚን (limen)፣ ሁኔታውን ደግሞ መሃል/ መካከል 'betwixt and between' ይሉታል፡፡ በመሆኑም በሽግግር ወቅት ያሉ ባለጉዳዮች ከማህበረሰቡ ውጭ በመሆናቸው ማንም በነሱ ላይ ስልጣን የለውም፡፡ በተለይም ባለጉዳዩ እንደ ቅዱስ የሚታይ ከሆነ እንዳይጎዳ ሲባል ከንክኪም ሊጠበቅ ይችላል (Van Gennep 1960)፡፡ በዚህ ወቅት ያሉ ባለጉዳዮችን ለማህበራዊ ዓለሙ የሞቱ ናቸው ይሏቸዋል (Turner 1967)፡፡ በዚህም ምክንያት ወቅቱ አስጊ እና አስጨናቂ ነው።

[18] ሰዎች ሽግግሩ ሊያስከትል ይችላል ብለው የሚያሳስቧቸውን ስጋቶችን ለመከላከል፣ ለማከም እንደ ሽግግሮቹ ዓይነት የተለያዩ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ይፈጽማሉ፡፡ የወሊድ ሽግግርን ስጋት ለመቀነስ ከእርግዝና ጊዜ ጀምሮ ነፍሰ ጡሯ ያማራትና፣ የሽተታትን በማቅረብና በመስጠት፣ በምጥ ጊዜ በተለይ በቤት ውስጥ ለሚያጋጥም ምጥ ቀላል ያደርጋል፣ ጊዜውንም ያሳጥራል ብለው የሚያምኑባቸውን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ይፈጽማሉ፡፡ ወንዶች ቀበቷቸውን ሴቶች መቀነታቸውን መፍታት፤ ቡና መቁላት፣ ድርሣነ ሩፋኤል መድገም፣ ወዘተ. በወቅቱ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ በሰላም ከተገላገለች እልልታው ቅቤ መቀባት፣ የማሪያም መሸኛ ገንፎ በተቻለ መጠን የደስታ ማብሰሪያ ክዋኔዎች ናቸው፡፡ ቀጥሎም እናትና ልጅ በአራስ ቤት የሚደረጉላቸው ጥበቃዎችና እንክብካቤዎች ዓላማ በደህና እንዲቆዩ ሲሉ የሚያከናውኗቸው ናቸው፡፡ ከዚያም በክርስትና ሥነ ሥርዓት በሙሉ ሰውነት ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ፤ ህጻኑም ከክርስቲያን ተራ ይቆጠራል፡፡ ወደ ጋብቻ ሽግግር ስሄድ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ አሁንም ድረስ ጋብቻ በልጅነት እድሜ የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው፣ በተጋቢዎች መካከል የቀደመ ትውውቅ አለመኖር፣ በተለይ የሴት ሚዜ አለመኖር ሙሽሮችም ሆኑ ቤተሰቦቻቸው ለጭንቀት ይዳረጋሉ፡፡ በመሆኑም በተለይ ሙሽሪት ተገዳ እንዳትደፈርና ጋብቻው አደጋ እንዳያስከትል በዋናነት ከሰርጓ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ በተከታታይ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች አሉ፡፡ ሙሽሪት ልታገባ እንደሆነ በሰርግ ዋዜማ ምሽት በሚፈጸም

### 6.8. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ከውሃ ጋር የተቆራኙ መሆናቸው

ውሃ በሶስቱም (ወሊድ፣ ጋብቻ እና ሞት) የሕይወት ሽግግሮች የለውጥ ማረጋገጫ እና ማወጃ ትዕምርት ሆኖ ተገኝቷል። እንዲሁም የባለጉዳዮችን ንጽህና እና ቅድስና ማብሰሪያ መሆኑ ተመላክቷል። ወሊድን ተከትሎ ወዲያው እናትም ልጅም በመታጠብ ጊዜያዊ ንጽህና ያገኙበታል። ቀጥሎም እናት በወለደች በአስረኛ ቀን የሃይማኖት አባቶች ውሃው ላይ ሥርዓተ ጸሎት በማድረግ (ወደ ጠበል በመለወጥ) እና በማጥመቅ በተወሰነ መልክ ወደ ማህበረሰቡ ትቀላቀላለች፤ በህጻኑ የክርስትና ቀን የሚጠመቅበትና ከክርስቲያን የሚያስቆጥረው አንዱ ተግባር ነው። ከዚህ በኋላ የእናት ንጽህና ታውጆ በሁሉም ማህበራዊ ሁነቶች መሳተፍ ትጀምራለች። በጋብቻ ወቅት ሙሽሮች የሰርግ ቀናቸው እየተቃረበ ሲሄድ በዋናነት ሁለት ቀን ሲቀረው ወይም በዋዜማ ሰውነታቸውን በመታጠብ ሙሽራ የሚያስመስላቸውንና የሚያደርጋቸውን ንጽህና ይጠብቁበታል። ሙሽራውና ሙሽሪት በአካል ከመተዋወቃቸውና በስጋ ከመገናኘታቸው በፊት የሙሽርነታቸው ማወጃ መታጠብ ነው። በሞት ወቅት አስከሬን ይታጠብበታል፤ ከቀብር በኋላም ለቀስተኛው በሙሉ እጁን እንዲታጠብበት በማድረግ የሞት ዳርቻ (መጨረሻ) እንዲሆን በመመኘት የሕይወትን ቀጣይነት ያስተምሩበታል።

### 6.9. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የተመሳሳይ ቁጥሮች መገለጫ ሁነቶች መሆናቸው

አንድ የሕይወት ሽግግር ከተካሄደ ጀምሮ ያሉት አርባና ሰማኒያ ቀናት የለውጥ ማላመጃ ጊዜ ናቸው። በቃለ መጠይቅ[19] የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው አንድ ህጻን ወንድ ከሆነ በተወለደ በአርባ፣ ሴት ከሆነች በሰማኒያ ቀን ክርስትና ይነሳሉ። ይህም ዓለምን ተቀላቅለውና ተላምደው እንዲቀጥሉ የሚያስችል የጊዜ ቆይታ ነው። ቀደም ሲል ሙሽሮች በጫጉላ ቤት የግድ ለአርባ ቀናት ከተላመዱ ደግሞ ለሰማኒያ ቀናት ይቆዩ እንደነበር ይነገራል ይህ የጫጉላ ቆይታ ተጋቢዎች እርስበርስ ተላምደው እንዲኖሩ የሚያመቻች ጊዜ ተደርጎ ሊታይ ይችላል። አንድ ሰው በሞተ በአርባኛው ቀን ትልቅ ሥርዓተ ክዋኔ የሚፈጸምበት የመታሰቢያ ቀን ነው። ሰማኒያም እንዲሁ ሌላው የሟች ነፍስ የመታሰቢያ ቀን ሆኖ ይከበራል። ሀዘንተኞችም እስከ አርባ ቀን ድረስ ማቅ ለብሰው፣ ገመድ ታጥቀው፣ ነጭ ክር አንቀው (በአንገታቸው አስረው)፣ ጸጉራቸውን ተላጭተው፣ ነጠላ ታጥቀው (አደግድገው)፣ ወንዶች የሀዘን ኮፍያ አድርገው፣ ጋቢ አጥፈው፣ ካፖርት ለብሰው ይቆያሉ። ቀደም ሲል እስከ አርባ ቀን ቀብሩ ላይ እየሄዱ ያለቅሱ እንደነበር ይነገራል። ይህም ሀዘኑ ከልባቸው እንዲወጣላቸው ያግዛል። ከአርባ ቀን መታሰቢያ በኋላ ግን ዋናው የሀዘን ጊዜ የሚያበቃበት በመሆኑ

---

ምሬ (አንዲት ልጃገረድ እስከ ሰርጓ ዋዜማ በወገቧ የምታስረው ከከብት ቆዳ የሚሰራ መታጠቂያ ሲሆን መኋላ በመቀነት ይተካል፡፡) የመፍታት ሥነ ሥርዓት እንድታውቅ ይደረጋል፡፡ በዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት፣ በምርቃት፣ ወዘተ. ከባለቤቷ ጋር ትተዋወቃለች፡፡ ቀጥሎም በጫጉላ ቤት በሚደረጉ ቀጣይነት ያላቸው ሥርዓተ ክዋኔዎች ለውጡን እንዲላመዱ ያደርጋሉ፡፡ በሞት ሽግግር ወቅትም ሰዎች እድሜያቸው እየገፋ፣ በሽታ እየበረታባቸው፣ ጉልበታቸው እየደከመ ሲሄድ ከፈጣሪ ጋር የሚታረቁባቸውን እንደ ንሥኃ መግባት፣ መቁረብ፣ መመንኮስ ያሉ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ተግባራት እየፈጸሙ ይቆያሉ፡፡ እነዚህን ተግባራት በማከናወናቸውም ከሞት በኋላ ያለውን ዘላለማዊ ዓለም እንወርሳለን ብለው ያምናሉ፡፡ ከሞት በኋላም ከዕለት እስከ ዓመት ባሉ የተለያዩ ቀናት የሚፈጸሙ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይፈጸማሉ፤ ዓላማቸውም ሟች እንድትጸድቅ ሲሆን በዚህ የሟች ቤተሰብ ይጽናናል (Siraye 2023)፡፡

[19] ቃለ መጠይቅ፣ ወ/ሮ ድንቃየሁ አለሙ፣ ዱምሪ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ ነዋሪ፣ የልምድ አዋላጅ እና ባህል አዋቂ እናት፣ በቀን 01/06/2012 ዓ.ም የተካሄደ

ወደ ቀልባቸው የሚመለሱበት እና ሕይወታቸውን ለማስቀጠል የዘወትር ተግባራትን ማከናወን የሚጀምሩበት ነው። ከላይ የተዘረዘሩት የሀዘን መገለጫዎችና ምልክቶችም እየቀለሉና እየቀነሱ ይሄዳሉ።

## 6.10. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የመስዋዕት ማቅረቢያ ሁነት መሆናቸው

በቃለ መጠይቅ[20] እና በምልከታ[21] የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መስዋዕት በወሊድ፣ በጋብቻና በሞት ወቅት የተለመደ ነው። መስዋዕቱም ዶሮ፣ በግ ወይም በሬ በማረድ የሚቀርብ ነው። በወሊድ ወቅት ምጥ ሲጠና ዶሮ በወላዷ ጭንቅላት ላይ አዙረው ያርዳሉ። በጋብቻ ወቅትም ገና ከሰርጉ ዋዜማ ጀምሮ የከብት እርድ ይፈጸማል። ቀጥሎም በመልስ ሥነ ሥርዓት ሙሽሮች በግ አርደው እንዲገቡ ይደረጋል። እዚህ ላይ የቀረበው መስዋዕት አላማ የተጋቢዎችን ቃል ኪዳን ለማጽናት፣ ትዳራቸው እንዲባረክና እንዲቀጥል ለማድረግ ነው።

በሞት ወቅትም በተለይ ሟች በእድሜ የገፉ ከሆነ አስከሬን ከቤት እንደወጣ ዶሮ ይታረዳል። ከዚያ በኋላ ግን በአርባ ቀን መታሰቢያ መቃብሩ ላይ በግ ይታረዳል። በሰማኒያ ቀኑም መጠነኛ በሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ክዋኔ ታስቦ ይውላል። የእነዚህን ሥርዓተ ክዋኔዎች መፈጸም ምክንያት ምን እንደሆነ ቄስ ይበሉ[22] የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል። ፈጣሪ አምላክ ነፍሱን እንዲምረው፣ በዚህ ዕለት የሟች ነፍስ ስጋው ባረፈበት (በተቀበረበት) ቦታ ትመጣለች እና እሷን ለማስደሰት ሲባል ይከወናል። በዚህም ምክንያት ለሟች ነፍስ መታሰቢያ እና ምኅረት ማስደረጊያ የሆኑ መስዋዕቶች መስዋዕት አዎንታዊ ትርጓሜ ይሰጠዋል። የሟች ቤተሰብም ጉድለቱን ተቀብሎና ለምዶ ሕይወቱን የሚቀጥል ይሆናል።

## 6.11. የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የጭንቀትና የስጋት ምንጭ መሆናቸው

በሕይወት ሽግግሮች ሂደት ዋናው ሽግግርና ለውጥ የሚካሄድባቸው የምጥ ጊዜ፣ የጫጉላ ጊዜና የእርጅና፣ የህመምና የድካም ጊዜ አስጨናቂ ናቸው። እነዚህ ቅጽበታዊ ሽግግሮች (በተለይ ወሊድና ጋብቻ) አዎንታዊ ይሁን አሉታዊ ውጤት እንደሚያስከትሉ በግልጽ አለመታወቁ፣ አንዳንድ ጊዜም የተጠበቀውን አዎንታዊ ውጤት ሳይሆን ያልታሰበና አሉታዊ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው ሌላው ጉዳዩን አሳሳቢ የሚያደርግ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ዋናውን ባለጉዳይ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡን ጭምር ለጭንቀት ይዳረጋሉ።

# 7. የሕይወት ሽግግሮች ትስስር

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ እምነትና እሳቤ መሰረት ወሊድ ሰውን ወደሚታየው ዓለም የሚቀላቅል፣ ጋብቻ ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚያሸጋግር እንዲሁም ሞት ስጋዊ/ዓለማዊ ሕይወት

---

20 ቃለ መጠይቅ፣ አቶ እንዳው ውብቴ፣ የሀገር ሽማግሌ እና ባህል/ታሪክ አዋቂ፣ በቀን 12/06/2012 ዓ.ም የተካሄደ

21 ምልከታ፣ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ገበሬ ማህበር፣ ምልከታው የተካሄደው በቀን 24/05/2012 ዓ.ም፣ ባህላዊ ሰርግ ላይ ነው፡፡

22 ቃለ መጠይቅ፣ ምርጫ ቦራቡር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ፣ የሃይማኖት አባት፣ ቃለ መጠይቁ የተካሄደው በቀን 15/06/2012 ዓ.ም ነው፡፡

የሚያበቃበትና ወደ ዘላለማዊ ዓለም የሚያሸጋግሩ የህይወት ሽግግሮች ናቸው። ወሊድ አንድ ሰው ሰው ሆኖ በሚታየው በዓለም የሚገለጥበት ሲሆን ሞት ደግሞ በተቃራኒው ነፍስ ከስጋ የምትለይበትና በዓለም በሕይወት መኖር የሚያበቃበት ነው። ሰው በዚህ ህልውናው ተፈጥሯዊ ሂደቶችን እያለፈ የኖረውን ያህል ኑሮ በስጋ ሞት ሕይወቱ ከዓለም ተለይታ በድኅረ ሞት ዘላለማዊ ወደሆነው ዓለም ትሸኛለች። ለዚህም በዓለም የመኖር ትርጉም፣ የወሊድና የሞት ጉዳይ የስጋ ባህሪ ተደርጎ ይታሰባል። ሕይወት ግን በቅድመ ወሊድ የነበረችና በድኅረ ሞትም የምትቀጥል ዘላለማዊት መሆኗ ይገለጻል። ጋብቻ ደግሞ በአንድ በኩል ሌላ አዲስ ደረጃን ያስተዋውቃል፤ በሌላ በኩል አዲስ ሕይወት ወደ ዓለም ለማምጣት መሰረት የሚጣልበት ነው። ከዚህ በመነሳት የምንኖርባት ዓለም ጸንታ የቆመችው በሰው ልጅ የሕይወት ሽግግሮች (ወሊድ፣ ጋብቻና ሞት) የማያቋርጥ ሂደትና ዑደታዊ ሽከርክሮሽ አማካኝነት ነው ማለት ይቻላል። የሕይወት ሽግግሮች በሰው ልጅ የዓለም (የስጋ) እና የሰማይ (የነፍስ) ነገረ ሥራዎች መሆናቸውን እንዲሁም እርስበርስ የተሳሰሩ እና አንዱ በሌላው ውስጥ የሚታይ፣ አንዱ ወደሌላው የሚያሸጋግር፣ የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም የሚያስተሳስሩ መሆናቸውን ማጤን ተችሏል።

## 8. *መደምደሚያ*

ይህ ጥናት በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች አከባበር ወቅት ተደጋግመው የተገለጡ የጋራ ትዕምርቶችን ከተግባራዊያን፣ ከተግባራዊ መዋቅራዊያን እና ከፍካሬ ልቡናውያን ንድፈ ሀሳቦች ውስጥ ተስማሚ የሆኑ ሀሳቦችን በመውሰድ ተንትኗል። በትንተናውም በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶችን (ወሊድ፣ ጋብቻ እና ሞት) ምክንያት በማድረግ በሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ተደጋግመው የተከሰቱ ትዕምርቶች ተፈትሸዋል። እነዚህም ትዕምርቶች የወከሏቸው ሀሳቦች፣ ቁሶች እና ሁኔታዎች በማህበረሰቡ የጋራ እሴትና እውቀት ላይ የተመሰረቱ፣ የተስማሙባቸውና የሚያስቀጥላቸው መሆናቸውን መረዳት ተችሏል። ይህም ሲባል አንድ ትዕምርት የወከለው ነገር በአንድ በተወሰነ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ/ውስጥ ብቻ ታይቶ የሚጠፋ ሳይሆን ሁሉም ሥርዓተ ክዋኔዎች በተከናወኑ ቁጥር የሚደጋገምና የሚቀጥል መሆኑን ያመለክታል። ከዚህም ባሻገር ትዕምርቶች የብዙ ሀሳቦችና ትርጉሞች ማደሪያ መሆናቸውን፣ አንድ ትዕምርት የወከለው ጉዳይ የተለያየ ግን የሚደጋገም መሆኑ አመላካች ነው። ፍካሬ ልቡናውያን እንደሚሉት ትዕምርቶች በሰው ልጅ ድብቅ የአዕምሮ ክፍል የተቀመጡ፣ የተረሱና የተተው ሀሳቦችና ስሜቶች ውክልና መሆናቸው የትዕምርቶችን ምንነት በመተርጎም ሂደት የተደረሰባቸው ጉዳዮች ያሳያሉ። ከዚህ ቀጥሎ ከላይ በቀረበው መሰረተ ሀሳብ የተቃኙ፣ በሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ወቅት ተደጋግመው የተገለጡ የጋራ ትዕምርቶች ቀርበዋል።

ሥርዓተ ክዋኔዎች በሶስቱ የመዋቅር ደረጃዎች (መለየት/መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል/ለውጥ) የሚያልፉ መሆናቸው ተስተውሏል። እንዲሁም የሕይወት ሽግግር ሥርዓተ ክዋኔዎች የማህበረሰቡ የጋራ እሴቶች የሚገለጡባቸው፣ የሚከበሩባቸውና የሚሰበኩባቸው ወሳኝ የሕይወት ዘመን ሁነቶች መሆናቸው ተረግግጧል። ተደጋግመው ከተገለጡ ትዕምርቶች መካከል መልካም ምግባር፣ ቀዳሚ የዘር ሀረግ፣ ጀግና፣ ሀገርና ሃይማኖት በአዎንታዊ መንገድ የተገለጹ ሆነው ተገኝተዋል። የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች የማህበረሰቡን መዋቅር መግለጫ፣ ማጠንከሪያና ማስጠበቂያ ሁነቶችም ናቸው። እነዚህ ሁነቶች በባህሪያቸው አስጨናቂ፣ አስጊና ለለውጥ የሚያጋልጡ ወሳኝ የሽግግር ወቅቶች በመሆናቸው ጥበቃና እንክብካቤ የማይለያቸውና ማህበረሰቡ በጋራ የሚያከብራቸው ጉዳዮች

ናቸው። ከዚህም ባሻገር የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች በማህበረሰቡ መካከል የተፈጠረ ጥላቻ እና አለመግባባት የሚፈታባቸው፣ እርቅ የሚፈጸምባቸው እና ሰላምን የሚያውጁ ሁነቶች መሆናቸውን መረዳት ተችሏል።

የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች መለየት/ መነጠል ማከበሪያ ሁነቶች ናቸው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በወሊድ ወቅት የእናትና የልጅን መለያየት፣ በጋብቻ ወቅትም ተጋቢዎች ከራሳቸውና ከአካባቢያቸው መለየት እንዲሁም በሞት ወቅት የሚች ነፍስ ከስጋ መለየት ምክንያት በማድረግ የሚከበሩ መሆናቸውን ማጤን ተችሏል። የሕይወት ሽግግሮች ከውሃ ጋር የተለየ ቁርኝት አላቸው። ውሃ የሕይወት ሽግግሮች የሚያስከትሏቸውን ለውጦች የሚያውጅ ትዕምርት ነው ማለት ይቻላል። በሕይወት ሽግግሮች ወቅት የተገለጡ የጊዜ ቆይታን የሚያመለክቱ ቁጥሮች የለውጥ መለማመጃ ጊዜዎች ተደርገው ሊታዩ ይችላሉ። ወሊድን ተከትሎ ወንዶች በአርባ፣ ሴቶች ደግሞ በሰማኒያ ቀን ክርስትና መነሳት፣ በጋብቻ እስከ አርባና ሰማኒያ ቀን በጫጉላ መቆየት እንዲሁም በሞት አርባና ሰማኒያ ቀን ድረስ ባለጉዳዮች ለውጡን እንዲላመዱ የሚያስችሉ ተደጋግመው የተገለጡ የጋራ ትዕምርቶች ናቸው።

በመጨረሻም የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ልዩ ልዩ አዎንታዊ አላማ ያላቸው መስዋዕት ማቅረቢያ ሁነቶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ በመነሳት የሕይወት ሽግግሮች የማህበረሰቡ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚገለጡባቸውና በማያቋርጥ ሂደት የሚያልፉ በመሆናቸው የማህበረሰቡን ስጋዊ እና መንፈሳዊ ዓለማት ያስተሳስሩ እንዲሁም ለሕይወትና ለዓለም ያለን አመለካከትና አስተሳሰብ መግለጫ የሆኑ ትዕምርቶች የሚገለጡባቸው ሁነቶች ናቸው የሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል።

## ማጣቀሻዎች


መለሰ ሙሉጌታ። (2000 ዓ.ም)። “ባህላዊ የወሊድና የገለብ ስነ-ሥርዓት ፎክሎራዊ ገጽታ በአክሱም ከተማ የክርስትና እምነት ተከታዮች”፣ በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የተካሄደ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻህፍት።* (1947 ዓ.ም)። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ሥራዬ እንዳለው። (2005 ዓ.ም)። “ዋና ዋና የሕይወት ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ”። በኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የተካሄደ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

አፀደ ተፈራ። (2007 ዓ.ም)። “የዋግ ኽምራ የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና”። በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ለማግኘት የተካሄደ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ደስታ ተክለወልድ። (1962 ዓ.ም)። *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት።* አዲስ አበባ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደስታ አማረ። (2007 ዓ.ም)። “የሕይወት ዑደት (የወሊድ፣ የጋብቻ እና የሞት) ሥርዓቶች ክዋኔ ትንተና በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ”። በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ለማግኘት የተካሄደ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ድርብወርቅ ብጹ። (2007 ዓ.ም)። “የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች በማንዱራ ወረዳ”። በፎክሎር የማስትሬት ዲግሪ ለማግኘት የተካሄደ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ዋልተንጉሥ መኮንን። (2007 ዓ.ም)። “ተፈጥሮን መናቅና ስጋን ማክበር ለክፉ ዓይን አጋላጭ ክስተት በምስራቅ ጎጃም በሚገኘው የጎዛምን ማህረሰብ ዕምነት”። በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ለማግኘት የተካሄደ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

Atkin, A. 2016. Peirce. New York.

Bell, Cathrine. (1997). *Ritual Perspectives and Dimensions*. Oxford University Press. New York.

Berger H. and Delnegro G. Bauman’s. (2002). Verbal Art and the Social Organization of Attention: The Role of Reflexivity in the Aesthetics of Performance. *Journal of American Folklore.*

Buchler, Justus. (1939). *Charles S. Peirce’s Empiricism*. New York, Harcourt, Brace, and Company.

Canda, Edward. R. (1988). Therapeutic Transformation in Ritual, Therapy, and Human Development, *Journal of Religion and Health,* Vol. 27, No. 3 pp. 205-220, Published by: Springer.

Creswell, John W. (2003). *RESEARCH DESIGN Qualitative, Quantitative. And Mixed Methods Approaches* (2nd Edition). University of Nebraska, Lin coln. Sage Publications, Inc.

Cohen, Percy. S. (1969). Theories of Myth. *Man, New Series*, Vol.4, No.3 pp.337-353). Royal Anthropological Institute of Great Britain and Ireland.

Crotty, Michael. (1998). *The Foundation of Social Research Meaning and Perspective in the Research Process***.** London, Thousand Oaks. New Delhi. Sage Publications, Inc.

Dawson, Catherine. (2007). *A Practical Guide to Research Methods* (3rd Edition), British Library Cataloguing in Publication Data.

Dorson, Richard M. (1972). *Folklore and Folklife: An Introduction.* Chicago. University of Chicago Press.

Firth, Raymond. (1973). *Symbols, public and private.* George Allen & Unwin Ltd, Routledge.

Freud, A. (1936). *The Ego and the Mechanisms of Defense*. Madison, CT: International Universities Press.

Gallie, W. B. (1952). *Peirce and Pragmatism*. Harmondsworth.

Gray, David. E. (2004). *Doing Research in the Real World***.** London. Thousand- Oaks New Delhi. Sage Publications.

Green, Thomas. A. (Ed.) (1997). *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.* Santa Barbara, California, Denver, Colorado, Oxford, England.

Greenlee, D. (1973). *Peirce's Concept of Sign*. The Hague.

Grimes, Ronald. L. (1943). *Deeply into the Bone Re-Inventing Rites of Passage.* Berkeley Los Angeles London: University of California Press.

Guday Emirie. (2005). "Early Marriage and Its Effects on Girls' Education in Rural Ethiopia: The Case of Mecha Woreda in West Gojjam, North-Western Ethiopia", Submitted for Doctorate/Doctoral Grade in Ethnology (Social and Cultural Anthropology) to the Faculty of Social Sciences, Georg-August University of Goettingen.

Jung, C.G. (1956). *Collected Works of C.G. Jung* Volume 5. *Symbols of Transformation,* Princeton University Press.

Kalmijn, Matthijs M. (2004). Marriage Rituals as Reinforcers of Role Transitions. *Journal of Marriage and the Family*. An Analysis of Weddings in the Netherlands. Tilburg University.

Kitahara, Michio. (1974). A Function of Marriage Ceremony. *Anthropologica, New Series,* Vol. 16, No. 2, pp. 163-175; Canadian Anthropology Society.

Kothari, C.R. (2004). *Research Methodology Methods and Techniques.* (2nd Edition), Jaipur (India): New Age International Ltd. Publishers.

Mazama, A. and Asante. M. (Eds) (2009). *Encyclopedia of African Religion.* United States of America: Sage Publications.

Myrvold, K. (2007). *Inside the Gurus Gate Ritual Uses Text among the Skins in Varanasi.* Sweden: University Lund.

Pentkainen, J. (1979). *The Symbolism of Liminality.* Scripta Instituti Donneriani Aboensis,

Salamone, Frank A. (Ed.). (2004). *Encyclopedia of Rites, Rituals and Festivals.* London: Routledge New York.

Segal, Robert A. (Ed.). (2006). *The Blackwell Companion to the Study of Religion***.** Australia, Blackwell Publishing Ltd.

Siraye Endalew. (2023). *Functions of Marriage Ritual in Jabi Tehinan District*. Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture (JAAL), Volume 12, Number 1.

Turner, Victor. (1974). *Dramas, Fields, and Metaphors: Symbolic Action in Human Society.* Ithaca, N.Y Cornell University Press.

Waskul Dennis and Vannini Phillip (Editors). (2006). *Body/Embodiment Symbolic Interaction and the Sociology of the Body*. England, Ashgate Publishing Limited.

Van Gennep, Arnold. (1960). *The Rites of Passage.* Translated by M. B. Vizedom and G. L.
Caffee. Chicago: University of Chicago Press. Originally published in 1909.